ጠርዝ በኩል ሆነው ነው እንዲሄዱ የሚደረጉት፡፡ ብዙዎቹ በባለቤቶቹ ኪሳራ የህይወት ዋጋ ነው የከፈሉበት፡፡ አንዱ አህያ ሁለት መቶ ማር ትሬዛ እንደተጫነ ተንከባሎ ከፊት ለፊቴ ወደቀ፡፡

ሙሉ የቀን ብርሃን ለለወጣ ፊት ለፊት ያሉት መንገደኞች መፍጠን ጀምረዋል ሆኖም በቂ አልነበረም፡፡ ለአቱ አየሮጠብን ነው፡፡ በድንገት የጩኸት ድምፅ እየተቀባበለ እንደላት ተቀጣጠለ

"መጣች" " መጣች"

ሁሉም ሰው መዝለል፤ ባለበት መቆም ፤ ትንፋሹን መያዝ ጀመረ፡፡ እውነት ነው እየደመቀ የሚመጣ የአውሮፕላን ድምፅ ይሰማኛል፡፡

ደጃዝማች ሁሉም ሰው የየራሱን እንስሳ ይዞ በፀጥታ እንዲቀመጥ እና እንዳይንቀሳቀስ ትዕዛዝ ሰጡ፡፡ ከድምፁ በስተቀር ምንም ላናይ በመረበሽ መጠበቅ ጀመርን፡፡ እዚህ መሮጫ ሜዳ ወይም መጠለያ በሌለበት ቦታ ላይ ይይዙን ይሆን? መቆረጫ የሌለው የሚመስል ረዥም ጊዜ ከቆየን በኋላ ሁለት ባለነጠላ ሞተር ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች አየን፡፡ ዝቅ ብለው ነበር የሚበሩት፤ እርፈንበት በነበረው የካምፕ ቦታ በኩል አድርገው ወደ ደቡብ አቅጣጫ ሄዱ፡፡

"ምንም ማየት አትችልም! እውር ነች!" በማለት ወታደሮች እርስ በርሳ ይነጋገሩ ነበር መንገዱን እንደገና ስንቀጥል፡፡ በኔ ግምት እነዚህ አልባሌ ጀግኖች የአውሮፕላን በምብ አልወረደብንም እና ምን እንደሚመስል እናውቅም ብለው ላያማርሩ አይቀሩም፡፡

ብዙም ሳንዘገይ ከለአት በኋላ ጠለሎ(ፀለሎ) ደረስን፡፡ ለሰውም ለእንሰሳውም ረዥምና አድካሚ ቁልቁል መንገድ ነበር፡፡ ለዚያን ቀን አድካሚ ጉዞ የመጨረሻው ወይም ማቆሚያችን ነበር፡፡



# ምዕራፍ ለባት

## ጭስ የሌለው እሳት

ጠለሎ ከባህር ወለል 1800 ሜትር በላይ ይገኛል፡፡ ከዋልድባ ትይዩ በተከዜ ረባዳ ቦታ የመጨረሻው ደንበር ላይ ነው፡፡ የተለያዩ የመሬት ገፅታዎቹ አጠር ካሉ ጫካዎችና ሰፋፊ ሜዳዎች ጋር ያማረና ለካምፓችንም የሚለማማ ሥፍራ አድርጎታል፡፡ ከላይ ከተራራው ተነስቶ የሚወርድ ትንሽ ወራጅ ንፁህና በቂ የመጠጥ ውሃ እንደልብ እንድናገኝ አድርጎናል፡፡

ዕይታው አስደናቂ ነው፡፡ የተከዜን ሸለቆ ማየትም እችላለሁ፡፡ ሸለቆው በደቡብ ምሥራቅ በኩል ከሰሜን ተራሮች ጀርባ ተነስቶ እንደ ትልቅ ገደል እየተጠማዘዘ ወደፊት በመሄድ ፀሀይ በለበለበውና ሰው በማይኖርበት ረባዳ መሬት አድርጎ በሰሜን በኩል በአምባ ብርኩታ ጀርባ ይለወራል፡፡ ካለንበት በቀጥታ በምሥራቅ በኩል ማዶው የትግራይ መሬት ነው፡፡ በጠራ ቀን በተለይ ከለአት በኋላ  የአድዋ ተራሮችን መለየት ይቻላል እነሱም በልጅነት ዘመኔ የድሮ ጓደኞቼ ሶሎዳ፣ ለማይታ እና አባ ገሪማ ናቸው፡፡

የዚህ ሥትራቴጂያዊ አቀማመጥ ጠለሎን ልዩ ያደርገዋል፡፡ ከዚህ ተነስቶ የወልቃይት ተራራ ሰንሰለቶችን በመከተል ባጭር ጊዜ ውስጥ ሰቲት መድረስ ያቻላል፡፡ ይህ አጭር ርቀትም በትግራይ ረባዳ መሬቶች አቋርጦ ሰቲት ከመሄድ ጋራ እኩል ነው፡፡ ነገር ግን በሁለቱም መንገዶች ወባው መታውቅ የሚገባው አለቻጋሪ ነገር ነው፡፡

የተከዜ ወንዝ ምንም አይነት እንቅፋት አይፈጥርም፡፡ ወንዙ ጎድሎ ስለነበረ አቋርጦ መሄድ ይቻላል፡፡ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሳደረገ ሰውም ከአውሮፕላን ጥቃት መደበቅ የሚቻልባቸው ጥሩ ቦታዎች አሉ፡፡ ሜዳዎችም ቢሆን የሚታጨድ የሚበቃ ሣር ሳላላቸው እንስሶችን ለግጦሽ መልቀቅ አያስፈልግም፡፡

ሌላው የጠለሎ ራቅ ብሎ መገኘት ጥቅም ደግሞ የኢጣሊያ አውሮፕላኖች በየቦታው ቢበሩም ያተኮሩት ካርታ ላይ በሠፈሩት መንገዶች ላይ ነው፡፡

እንደ ቦታው ርቀት ደግሞ ጉዳቱ የመንገዱ መጥፎ መሆን ነው:: እንደዚህ አይነት መጥፎ መንገድ አይቼ አላውቅም:: ከፍየል መሄጃ መስመር የከፋ ነው:: በመንገድ ምክንያት ብዙ እንስሶች ነው ያለቁብን:: ጥቂቶቹ በገደሉ ተንከባለሉ ሌሎቹ ደግሞ የከፋ ቁስል ወጣባቸውና በዚህ ምክንያት ደካማና አገልግሎት የማይሠጡ ስለሆኑ መወገድ ነበረባቸው::

ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ከሰአት በኋላ ሲሆን ጠለሎ ደረስን:: ማምሻው ድረስ መድሃኒት ያለበት ጓዝ ሳላልደረሰ መጨነቅ ጀመርኩ::

ወይ ጠፍቷል ወይ ደግሞ በገደል ተንከባሎ ወድቋል ብዬ ማታውኑ ለደጃዝማች ተናገርኩ:: ወድያውኑ ሁለት ሰዎች በጥዋት ተነስተው እንዲሄዱና ሁኔታውን እንዲያጣሩ ትዕዛዝ ሰጡ:: የሚቀጥለው ቀን ማምሻ ድረስ ምንም የተሰማ ወሬም የለም:: ከደጃዝማች ጋራ ቁጭ ብዬ አያለሁ ፈጠነ መጥቶ ጓዙ እንደደረሰና ተራግፎ ከኔ ድንኳን አጠገብ እንደተቀመጠ ነገረኝ:: አነጋገሩ ግን ያልሆነ ነገር እንዳለ እንድጠራጠር አደረገኝና ለማጣራት ወጥቼ ሄድኩኝ::

እንደፈራሁት ሆነ::

በድንጋጤ ፈዘዝኩኝ:: ሣጥኖቹ ተሰባብረው መሬቱ ላይ ተበትነዋል:: አንዳንዶቹም የተሰባበረውን አንድ ላይ ለመያዝ በገመድ ታስረዋል:: የተቀዳደዱ ከረጢቶች በየቀዳዳው ከዚህ በፊት ንፁህ የነበሩ የጥጥ ጥቅሎች ብቅ ብቅ ብለው ይታዩበታል:: የእስትራ ፋርማሲ የሠራቸው ጥሩ የቁስል ማሸጊያዎች ተቀዳደው በየቦታው ወድቀዋል:: ትልቅ ዚንክ ሳልፎ የሚባል መድሀኒት በውስጡ የነበረበት የቆርቆሮ መያዣ ተሰብሮ ከዳን አልባ ሆኖ ይታያል:: የቆርቆሮ ሣጥኖች ተቀደው ውስጣቸው የነበሩ የቆርቆሮ ጣሳዎች ተከፋፍተዋል:: ትንንሽ ሣጥኖች ተሰባብረዋል:: የህክምና መሳሪያዎችና መድሃኒቶች እንደ ኩዊኒን፣ አስፒሪን ከኒኖች፣ በሙቶ የሚቆጠሩ በመርፌ የሚሰጡ መድሃኒቶች ጨምሮ በየቦታው ተበትነዋል:: የቁስል መጠቅለያ ማሸጊያዎች ተከምረዋል። አየሩ በአዮዲን ሽታ ታውዷል:: በውስጣቸው አልኮል፣ ካስተር ኦይል እና ሌሎችም ፈሳሾች የነበሩባቸው ብዙ የመድሃኒት ጠርሙሶች ባዷቸውን በሣጥን ውስጥ ተደርድረዋል::

ቁጭ ብዬ አነባሁ:: በመድሃኒትና የህክምና መሣሪያ ባለማግኘት ምክንያት ሌሎችን ሰዎች መርዳት ካልቻልኩ እራሴን ለአደጋና ለጦርነት ሽብር የማጋልጠው ለምንድን ነው? የቀይ መስቀል አምቡላንስ አባል አይደለሁም:: ብሆን ኖሮ በጠፋው መድሃኒትና መሳሪያ ትክ መጠየቅ እችል ነበር:: እነዚህ



መድሃኒቶች ለኔ በጣም ትልቅ ነበሩ:: ምክንያቱም እነዚህን መጠነኛ መድሃኒቶችና የቁስል መጠቅለያዎች ለማግኘት እንኳን መታገልና መለመን ነበረብኝ::

ይህ ጣጣስ እንዴት ሊፈጠር ቻለ?

መስፍንቶ በተባለ ቦታ መድሀኒቱን የተጫኑ አህዮች ልቅ ሆነው ተመልሰው ወደ አዲ አትየ ፈርጥጠው ተመልሰዋል:: ሰዎች እየሮጡ ተከተሏቸው፤ ከደረሱባቸው በኋላ ማታውኑ እዛው ማደር ነበረባቸው:: በመሳፍንት ጉትት ያደረባቸው ልጆች ወደ ታደረበት የካምፕ ቦታ ሲመጡ ወድቀው የቀሩ ሣጥኖችን ያገኛሉ:: ልጆችም የማይረባ ነገር ቢሆን ነው የተጣለው በማለት የሣጥኖችን ቁልፎች በድንጋይ ይሰብራሉ::

የነዚህ ሣጥኖች መገኘት ዝና እንደነፋስ በመንደሩ ወድያው ይደርሳል:: አባትና እናት ቤተዘመድ እየሮጡ ቦታው ይደርሳሉ:: በዚህ ራቅ ባለ ቦታ የቆርቆሮ ሣጥኖች፣ የቆርቆሮ ጣሳዎች፣ ጠርሙሶች፣ ቢላዋዎች እና መቀሶች የሚፈለጉ ነገሮች ናቸው:: ጥጡን እንኳን ሳይቀር ሴቶቹ ለፈትል ጥሩ ሆኖ አገኙት::

ጓዙን ሲያጅቡ የነበሩ ሰዎች ወደ ቦታው ሲመለሱ የሆነውን ነገር ሲያዩ ለራሳቸው ቢፈሩ እንግዳ ነገር አልነበረም:: ከረዥም ውይይት በኋላ ሁሉንም ነገር እዛው ትተው ወደ የቤታቸው ለመሸሽ ወሰኑ::

ለዚያን ቀን ማታ ግን በቦታው ሲያድሩ ከደጃዝማች እያሌው የተላኩት ሁለት ወታደሮች ከንጋቱ ላይ ከተፍ ይሉባቸውል:: ወታደሮችም በየቤቱ እየተዘዋወሩ ማግኘት የቻሉትን የተዘረፈ ዕቃ ሰበሰቡ:: ሶስት ሽማግሌ ገበሬዎች፤ ሁለት ሴቶችና አራት ልጆቻቸን ድንገት ደጃዝማች መቅጣት ከፈለጉ በማለት ይዘዋቸው መጡ::

ቅጣትም አልተሠጠም:: እንደነዚህ ያሉ የማያውቁ ሰዎችን ምን ማድረግ ይቻላል? መተካት የማይቻሉ መድሃኒቶችን ግን አበላሹ::

እስረኞቹም በነፃ ሲለቀቁ ነበር:: ዘመዶቻቸው ግን የተያዙትን ሰዎች እንዲለቀቁ እኔ ደጃዝማችን ካላማለድኩ በሕይወቴ ላይ አደጋ እንደሚያደርሱ ዛቱ:: ለዚህ ድፍረታቸው ሲባል ከኛ ጋራ ወደ ቆላው የአንድ ቀን የእግር መንገድ እንዲሄዱ ተደረገ::

በኔ በኩል የተበተነውን ጓዝ አንድ መልክ ለማስያዝ ሶስት ቀን ፈጀብኝ:: ያሳዘነኝ ነገር ግን ከነበረኝ መድሀኒትና ቁሳቁስ ግማሹ ነው የቀረኝ::

ጥዋትና ማታ እየተመላለሱ የሚጎበኙን የኢጣልያ አውሮፕላኖችን በየቀኑ ማየት እየተለመደ መጥቷል፡፡ ብዙ ጊዜ የሚታዩት ከአምባ ብርኩታ ወደ ሰሜን ወይም ከዚያ ሲመለሱ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ በኛ ላይ ዝቅ ብለው ይበራሉ፡፡ እንደሱ በሚያደርጉበት ጊዜ ቁጭ እንላለን፡፡ አይተውን ይሆን? ያለንበትን ቦታለ ወሬ አግኝተው ይሆን? ብለን እናሰባስን፡፡ ያም ቢሆን አይገርመንም ካምፓችን ውስጥ ብዙ ሰላዮች ነበሩ፡፡ በየቀኑ አንድ ወይም ሁለት ሰላዮች ይያዛሉ፡፡ ብዙ ጊዜ ነፃ የተሰቀቁ አገልጋዮች ወይም የገበሬ ልጆች ናቸው፡፡ ብዙም ጊዜ ያልበሰሉ ሰዎች ስለሆኑ ብዙም ትኩረት አንሠጣቸውም፡፡ በቀላል መንገድ የሚያውቁትን እንዲናገሩ ማድረግና በዛኛው ወገን የሚሆነውን ማወቅ ይቻላል፡፡

አንዱ ግን ከሌሎቹ በስተ ያለ ነበር፡፡ ወደ ካምፑ ሲመጣ መነኩሴ መስሎ መጣ፡፡ የቆዳ ቆብ ጭኖ፤ ትልቅ የብረት መስቀል በእጁ ይዞ መፅሀፍ በቆርቆሮ ሣጥን አድርጎ ከጎኑ አንጠልጥሏል፡፡ ነገር ግን ሳያስበው በአንድ በጠረጠረ ወታደር የያዘውን መፅሀፍ እንዲያነብ ሲጠየቅ ዕጣ ፋንታውን አገኘ፡፡ መፅሀፉንም ማንበብ አልቻለም፡፡ ወታደሩም ከዳጃች አያሌው የመቶ ብር ሽልማት ተቀበለ፡፡ የሚገባውም ነበር፡፡

እነዚህ ሁሉ ሰላዮች መገደል ወይም መሰቀል ነበረባቸው፡፡ ደጃች አያሌው ግን ሁሉንም ወደ ዳባት እየላኩ በአሰር ቤት እንዲማቅቁ አደረጓቸው "ለነዚህ አህዮች ገመድም ሆነ ጥይት አላባክንም ከዚያ ለተሻለ ነገር አጠቀምበታለሁ" ይሉ ነበር ደጃዝማቹ፡፡

እያንዳንዱ ሰው የካምፑን ቦታ ላለማጋለጥ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡ በራሳችን ሰላዮች እንደተረዳነው ጣልያኖቹ ያለንበትን ቦታ እስካሁን አላወቁም ግን ወደፊት የሚሆነው አይታወቅም፡፡ ሃምሳ ጠባቂዎች በካምፑ ውስጥ በየቦታው ተመድበው ከብቶች እንዳይለቀቁ እና በቀን እሳት እንዳይነድ ይቆጣጠራሉ፡፡

በአንድ አጋጣሚ አንደኛው ጠባቂ አንድ የወታደር መኮንን ይዞ በአኩለ ቀን ወደ ደጃች አያሌው መጣ፡፡ ትንሽ የጭስ መጠን በመኮንኑ ድንኳን ታይቷል፡፡ መኮንኑ ሲጠየቅ ደግሞ እውነት ነው አገልጋዩዋን ቡና እንድታፈላ ትዕዛዝ ሠጥቻለሁ ብሎ አብራራ፡፡ ነገር ግን ጭስ እንዳይኖርም ትዕዛዝ መስጠቱን ተናገረ፡፡



"ታዲያ አገልጋይዋ እሳት አላነድም ብትል ምን ታደርግ ነበር?"

"እገርፋት ነበር"

"እሳት ያለጭስ አይተህ ታውቃለህ ወይ?"

"የለም አይቼ አላውቅም"

"ታዲያ እንዴት ያን አይነት ነገር እንድታደርግ አገልጋይዋን ትጠይቃለህ?"

"እዝዣታለሁ የታዘዘችውን መፈፀም ሥራዋ ነው፡፡ ይህች ደደብ አህያ!"

"አህያ ከሆነችማ ሊገባት ስለማይችል ሀላፊነቱን አንተው ራስህ መውሰድ አለብህ፡፡ በግዴየለሽነትህ የመላው ካምፑን ህግ ተላልፈሃል፡፡ ስለዚህ ለዳኝነት ወደ ሠራዊቱ ፍርድ ቤት አሳልፌ ሠጥቸሀለሁ" የደጃዝማች ውሳኔ ነበር፡፡

ማምሻውኑ ሜዳ ላይ ሰዎች ዙርያውን ተሰበሰቡ፡፡ ደጃች አያሌው በግራና በቀኝ ጎናቸው ሌሎች ሽማግሌዎችን በማስቀመጥ መሀል ላይ ቁጭ አሉ፡፡ እጥፊው ተጠራና ለሁሉም እንዲሰማ ያጠፋው ጥፋት ጮክ ተብሎ ተነበበ፡፡ ደጃች አያሌው ምልክት ሲሠጡ ከሁሉም በእድሜ የገፉት የሰማንያ አንድ አመት እድሜ ያላቸው ፊታውራሪ እሉላ ከመቀመጫቸው ተነስተው የሚከተለውን መግቢያ ንግግር አደረጉ፡፡

"ሌሎች ላይ ዳኝነት የሚሠጥ ሰው ራሱ ይዳኝ፤ እጥፊው በሰይፍ ይቀጣ፤ የንጉሥ ጠላት ካለና ከቀረበ ለፍርድ ቀርቦ በሰይፍ በሞት ይቀጣ፤ ከለለ ደግሞ በፀሎት ይሁን፡፡ ዛሬ ትክክለኛውን ፍርድ እንድሠጥ ይርዳኝ"

ከዚያም ራሳቸው በገባቸው መንገድ እጥፊው ያደረሰውን በደል ከዘረዘሩ በኋላ ወደ ተቀመጡት ዞር ብለው

"በድሏልና ይቀጣ" አሉ

ሃምሳ የተለያዩ ሰዎች እየተነሱ ተመሳሳይ ሃሳብ ሠጡ፡፡ እኔም ብሆን ሃሳብ እንድሠጥ ተጠየቅሁኝ፡፡ እኔ ግን ጉንፋን ይዞኛልና ድምፄ ሻክሯል ብዬ ሃሳብ እንደማልሠጥ አሳወቅሁኝ፡፡ ይህ ጉንፋን ሲይዘኝ በመላው ጦርነት ጊዜ የመጀመሪያ ነበር፡፡ ሁሉም ሰው አስተያየቱን ከጨረሰ በኋላ ቅጣቱ ምን እንደሚሆን ውይይት ተጀመረ፡፡ መጨረሻም እጥፊው አርባ ጅራፍ እንዲገረፍ ተፈረደበት፡፡

በእንደዚህ አይነቱ ፍርድ ቦታ ሁልጊዜ ጠንካራ አገልጋይ ከቆዳ የተሠራ ጅራፍ ይዞ ይቆማል፤ ሶስት ገመድ የያዙ ረዳቶችም አብረውት ይገኛሉ፡፡ ፍርዱ እንደተወሰነ ወድያውኑ ሶስቱ ረዳቶች ወደ ተፈረደበት ሄደው የለበሰውን ልብስ ከሱሪው በስተቀር አስወለቁት፡፡ ከዚያም መሬት ላይ በሆዱ አጋድመው

እጆቹን ሰየብቻ፤ እግሮቹን አንድ ላይ አስረው በየቦታቸው ፈንጠር ብለው እያንዳንዳቸው አንዳንድ ገመድ ወጥረው ያዙ፡፡ ይህ ሁሉ በጥቂት ሰከንዶች ውስጥ ነው የተደረገው አጥፊውም መሬት ላይ በሆዱ ተኝቷል፤ እንዳይንቀሳቀስ በመስቀል ቅርፅ በገመድ ተወጥሯል፡፡

ገራፊው ጅራፉን እያወዛወዘ መጣ፡፡ ከታሰሩት እግሮች በኩል አንድ ሜትር ራቅ ብሎ ቆመ፡፡ የያዘው ጅራፍ ከበሬ ቆዳ የተሠራ ጉንጉን የሁለት ሜትር ርዝመት አለው፡፡ ወፈር ብሎ ይጀምርና ወደ ጫፉ እየቀጠነ ይሄዳል፡፡ አሥራ አምስት ሴንቲሜትር ርዘመት ያለው የአንጨት እጀታ ላይ ጠበቅ ብሎ ታስሯል፡፡

“ጠሽ!” የሚል ጩኸት ጅራፉ አየር ላይ ሲወነጨፍ በሚያሰማው ድምፅ ተከትሎ ጅራፉ ያሰምህረት የሰውየው ጀርባ ላይ ከትከሻው እስከመቀመጫው ባለው ሥፍራ ላይ ያርፋል፡፡ ወዲያውኑ ጅራፉ ያረፈበት መሰመር ማበጥ ይጀመርና ሰምበር መታየት ይጀምራል፡፡ ቆዳው መከፈት ሲጀምር ደም መታየት ይጀምራል፡፡




የተቀጣ ሰው በአደባባይ አርባ ጅራፍ ሲገረፍ (ምሥጋና ለፋሲል ጊዮርጊስ). from the book The City & Its Architectural Heritage Addis Ababa 1886 – 1941)

ጅራፉ ሲያርፍ ማየትና መስማት አሰቃቂ ነው፡፡ እንዳችም ድምፅ ከሰውየው አልተሰማም፡፡ በጣም ኩሩ ሰሰነበር ድምፅ ማሰማት አልፈለገም፡፡ ሌላ ጊዜ ግን ጅራፍ ባረፈበት ቁጥር የሚጮህና ምህረት የሚለምን ሰው ማየት የተሰመደ ነገር ነው፡፡



ሰላሳ ዘጠኝ ጊዜ ከተገረፈ በኋላ አርባኛው መሬት ላይ እንዲያርፍ ይደረጋል፡፡ ይህም ከፉ መንፈሶች ወይም መናፍስትን ለማስፈራራት ነው፡፡ የታሰረበት ገመድ ተፈታና የተገረፈው ሰውየ ተነስቶ ደጃዝማችን እጅ ነሳ፤ በጓደኞቹ ተደግፎም ወደ ቦታው ሄደ፡፡ ጥፋቱን ተናዞ በጦር ሜዳ ጓደኞቹ የተሠጠውን ፍርድ ምንም ሳያቅማማ ተቀብሏል፡፡ ቅጣቱን እንደ ወንድ ነው የተቀበለው፡፡ ይህ ሰው ባላምባራስ ተሰማ ይባላል፡፡ በኋላ እንዳወቅነው ከሆነ ውነተኛ ጀግና ሰው ነበር፡፡

በሀዳር ሶስት ከራስ እምሩ የተላከ ደብዳቤ ደረሰን፡፡ ደብዳቤው ራስ እምሩ ዳባት መድረሳቸውን ይገልፃል፡፡ ፊታውራሪ መርሶ በአባታቸው ስም ሳበረከቱት 150 በሬዎች ደጃች አያሌውን እንደሚያመሰግኑ ጠቅሶ ራስ እምሩ በተሠጣቸው ትዕዛዝ መሠረት ወደ ምሥራቅ በኩል በሰሜን ተራሮች አድርገው ወደ ተምቤን በመሄድ የራስ ካሳን ጦር እንደሚቀላቀሉ ነው፡፡




ልዑል ራስ እምሩ

ይህ ደግሞ ፈፅሞ ያልተጠበቀ ነገር ነበር እኛም ወደ የትኛው አቅጣጫ እንደምንሄድ ማሰብ ጀመርን፡፡ ወደ ሰቲት እንድንሄድ ትዕዛዝ ከተሠጠን ወደ

ሽሬ ግንባር ማን ሊሄድ ነው? ያ ደግሞ ለጣልያኖች የሚመች ቀዳዳ ይከፍታል፡፡ በሰላዮቻችን መረጃ መሠረት ጠላት በተከዜ ሸለቆ ዳር ዳር እራት የተለያዩ በታዎች ላይ መሽጎ ተቀምጧል፡፡ በተጨማሪም ወደ እከሱም በሚወሰደው መንገድ ሶስት ምሽጎች እዘጋጅቶእል፡፡ ታዲያ የሽሬ ግንባር የኛ ድርሻ ይሆን?

እንደዛ ከሆነ ደግሞ ጠቅላላውን የደንበር መሬት ለቲትን ማን ሊጠብቅ ነው?

ራስ ካሳ ከዘጠና ሺ ወታደሮቻቸው ጋራ የራስ እምሩን ርዳታ ማግኘት የሚያስፈልጋቸው አይመስልም፡፡ በዚህ ምክንያት ይህ አሰላለፍ ግራ የሚያጋባና እንግዳ ነገር ነው ብለን ያሰብነው፡፡ ማድረግ የምንችለው ነገር ቢኖር እዲስ እበባ ያሉ እዛዦች የሚያደርጉትን የሚያውቁ የጅል ሥራ የማይሰሩ ይሆናሉ ብለን ተሰፋ ማድረግ ነው፡፡

ደጃች እያሌው መልከተኛውን
"ራስ እምሩ ብዙ ሰው እላቸው?" ብለው ጠየቁ
"ቁጥር ሰፍር የሌለው እንደአንበጣ"
"ጥቢቃን በሚመለከት እኛ እንደምናደርገው ታደርጋላችሁ ወይ?"
"የለም፡፡ ሜዳ ላይ ነው ካምፕ የምናደርገው፤ የምንጓዘውም በቀን ነው"
"እንዴ ጣልያኖች ቢያዩዋችሁና በምብ መጣል ቢጀመሩባችሁስ?"
"እግዜር ያውቃል"

በሚቀጥለው ቀን በጥዋቱ ደመቅ ያለ የእውሮፕላን ድምፅ ሰማን፡፡ ወደ ዳባት እቅጣጫ ነበር የሚሄዱት፤ ቀጥሎም የፍንዳታ ድምፅ መሰማት ጀመርን፡፡ ሩቅም ቢሆን እስከ እኩለ ቀን ድረስ ድምፁ ይሰማ ነበር፡፡

ማምሻውኑ ቀረብ ካለው ወደ ምእራብ 20 ኪሎ ሜትር ርቀት ከሚገኝ ስልክ ቤት በመጣው መልከት የራሰ እምሩ ጦር ዳባት እውሮፕላን ማረፊያ እጠገብ ሜዳው ላይ በአሥራ ሁለት የኢጣልያ አውሮፕላኖች በቦምብ መደብደቡን ሰማን፡፡ ከመቶ ሃምሳ በላይ የሚሆኑ ቦምቦች ተጥለዋል፡፡ ከሚታወቀው 18 ሰዎችና ብዙ እንሰሳት ተገድለዋል፡፡ የጉዳቱ ሙሉ መጠን ግን ገና አይታወቅም፡፡ በጦሩ ላይ ያደረሰው የእእምሮ ሽብር ከፍተኛ ነበር፡፡ ሰዎችም ለነዚህ የሰማይ ላይ ጭራቆች በቂ መከላከያ የለንም ብለው ማማረር ጀመሩ፡፡

ከደጃዝማች እያሌው ጦር ጋር በመሆኔ እግዚእብሔርን እመሰገንኩ፡፡





የዳባት ከተማ በአውሮፕላን ሲደበደብ በኢጣልያኖች የተነሣ ፎቶግራፍ

የኢትዮጵያውያን ዘማቾች አይተው የማያውቁትን የአውሮፕላን ድብደባ በሚከተለው መንገድ ነበር የገለጡት (ከተርጓሚዎች)

በትግራይ ቢመጣ መች ይገባ ነበር
በጎንደር ቢመጣ መች ይገባ ነበር
በሸዋ ቢመጣ መች ይገባ ነበር
በጎጃም ቢመጣ መች ይገባ ነበር
በሰማይ ላይ መጣ በማናውቀው አገር

ያን ቀን ማምሻውን ከዳባት የተላከ የንጉሡ ደብዳቤ ደረሰ፡፡ አንድ ቀን ቀደም ብሎ በአውሮፕላን ነበር ወደ ዳባት የተላከው፡፡ ደብዳቤው የንጉሠ ነገሥቱ ማህተም አሰበት፡፡ ደጃች አያሌው በአስቸኳይ ወደ ሽሬ ግንባር እንዲንቀሳቀሱ ትዕዛዝ ተፅፎበታል፡፡ ራስ አምሩ ደግሞ አንደ ጦር አዛዥ ከአምስት ሺ ሰው ጋር ወደ ደጃዝማቹ መስፍን በመላክ የሰቲትን ድንበር እንዲጠበቅ እንዲያደርጉ ታዘዋል፡፡ በዚያ በኩል ጣልያኖች የማጥቃት ምልክት አላሳዩም፡፡ በቦታው ወታደሮች አላሰባሰቡም፡፡ ሰስዚህ ከላይ  የተጠቀሱት ሰዎች አሰላለፍ ሰጊዜው በቂ ነው ተብሎ ተገምቷል፡፡

ደጃዝማች ወድያውኑ በመላው ካምፕ ሰሚቀጥለው ቀን ዝግጅት እንደሚደረግና ጠመንጃና ጥይት እንደሚታደል እንዲታወቅ አሰደረጉ፡፡

ከአምስት ሺ ወታደሮች ጋራ በወልቃይት ተራሮች ለተቀመጡትና የሰሜኑን ድንበር ለሚጠብቁት  ለደጃዝማች አያሌው ታላቅ ልጅ ለፊታውራሪ ዘውዱና ለፊታውራሪ ሙላው ደብዳቤ ተላከ፡፡ በደብዳቤውም ወድያውኑ ወደ ምሥራቅ ተጉዘው የተከዜ ገባር ወንዝ ከሆነው ዛሬማ ወርደው እንዲጠብቁን ነው፡፡

የደጃዝማች አያሌው ተወካይ ፊታውራሪ ተሻገር ከ2500 ወታደሮች ጋር በመሆን ቀዳሚ ወይም የግንባሩን ጦር እንዲመሩ ታዘዙ፡፡ በሌሊት ከካምፕ ተነስተው ከዋናው ጦር የአንድ ቀን የአግር መንገድ ርቀት ቀድመው እንዲሄዱ ሆነ፡፡ ሙሉ ጨረቃም ሰለነበር ቁልቁል ገደሉን ወርዶ ለመሄድ ቀላል ሆነ፡፡ በችኮላ የኩዊኒን መድሃኒትና የመጀመሪያውን የመድሃኒትና እርዳታ መሰጫ ሻንጣ ሰሁለት የጦር ክፍሎች እንደሚሆን አድርጌ አዘጋጀሁ፡፡

ያን ቀን ማታ ብዙ እንቅስቃሴ በካምፑ ወሰጥ ነበር፡፡ ጫጫታና ሳቅ በየቦታው ይሰማ ነበር፡፡ ሁሰት ሺ የሚሆኑ ወታደሮች በዛው ልክ የሚሆኑ ሴቶች ልጆችና አገልጋዮች ከዘመዶቻቸውና ጓደኞቻቸው ጋራ ሲሰነባበቱ የተፈጠረ ነው፡፡ በሺ የሚቆጠር እሳት በየቦታው እየነደደ ለካምፑ ተጨማሪ ብርሃን ሠጥቶታል፡፡ የመጨረሻው ስንብት እንዳለቀ የቀሩት ወደ የቦታቸው ሲሄዱ እሳቱም ተራ በተራ እንዲጠፋ ተደረገ፡፡ መጨረሻም ቀዝቃዛዋ ጨረቃ ብቻ ለካምፑ ብርሃን ሆነች፡፡






ወደ ጦር ግንባር የሚሄዱ የኢትዮጵያ ዘማቾች ቤተሰቦቻቸውን ሲሰናበቱ በሐረር ግንባር



# ምዕራፍ ስምንት

## የሠራዊቱ ግምገማ

የስሜን ቆዳ ስፋት ወደ ሰላሰ አምስት ሺ ካሬ ኪሎ ሜትር ነው ተብሎ የሚገመተው። የህዝብ ቆጠራ ተደርጎ ስለማይታወቅ የነዋሪውን ቁጥር ማወቅ አስቸጋሪ ነበር። በደጃዝማች አገዛ በኔ ሰሌት ቁጥሩን ከሶሰት መቶ ሺ እስከ አራት መቶ ሺ አድርጌዋለሁ።

የስሜን ግዛት በስድስት ክፍሎች ይከፈላል። በሰላም ጊዜ እነዚህን ክፍሎች የሚያስተዳድሩ ገዥዎች በጦርነት ጊዜ ደግሞ የጦር አዛዥ ይሆናሉ። የሁሉም ማዕረጋቸው ፊታውራሪ ነው። ፊታውራሪ ከኮሎኔል ጋር የሚስተካከል ማዕረግ ነው። ከፍ ያለው ማዕረግ ደጃዝማችነት ነው ግን እያሌው ራሳቸው ደጃዝማች ስለሆኑ ለሌሎች መስጠት የሚችሉት ፊታውራሪነቱን ነው።

የስድስት ክፍሎች ጠቅላላ ሠራዊት ብዛት ወደ 13500 ሰዎችን ያጠቃልላል። በዚህ ቁጥር ላይ 1500 የሚሆኑ የጥበቃ ወይም የቀኝ ዘበኞችና 1000 የሚሆኑ በፊታውራሪ መርሶ የሚታዘዙ የዳባት ከተማን ስርአትና ደንብ የሚያስጠብቁ ይጨመርበታል።

የቀኝ ዘበኞች በቆዩና በሰለጠኑ ታማኝ በሆኑ በሰላም ጊዜ ቋሚ ጦር ሆነው የሚያገለግሉ ወታደሮች የተመሰረተ ነው፡ ይህ ጦር ለዳጃች እያሌው ጥበቃና ህይወት ሀላፊነት አለበት። ትጥቅን በሚመለከት ዘመናዊ መሳሪያም እንደ መውዜር፣ ሊ መትፎርድ እና ማንሊቸር፣ አራት ከባድ አውቶማቲክ መሳሪያዎች፣ አስር ቀለል ያሉ አውቶማቲክ መሳሪያዎች ከበቂ ጥይት ጋራ የታጠቁ ነበሩ። የሚከበሩ ጠባቂዎች ናቸው። ከሌሎች ወታደሮች የሚለዩት እነዚህ ዘበኞች ተብለው ስለሚጠሩና ከመላው ጦር የወታደር ዩኒፎርም የሚለብሱ እነሱ ብቻ ስለሆኑ ነው።

የእዝ ሰንሰለቱ የተወሳሰበ ነው። ምክንያቱም በአብዛኛው የሚከተለው ህግ ወይም ደንብ ስላልነበረው ነው። ለምሳሌ እንደ ኮሎኔል የሚቆጠረው



ፊታውራሪ መቶ ሰዎች ብቻ ሊያዝ ይችላል ይህ ደግሞ ከንጉሡጋራ እንዳለው ቅርበት ወይም ሽረት ሊሆን ይችላል። ወይም የትንሽ ከተማ ገዢ ይሆንና በቂ የሰው ቁጥር ላያሰልፍ ይችላል። ባጠቃላይ የማእረግና የሚያዟቸው ሰዎች ቁጠር እንደሚከተለው ነው።

| | |
|---|---|
| አስር አለቃ | የ25 ሰው አዛዥ |
| አምሳ አለቃ | የሀምሳ ሰው አዛዥ |
| መቶ አለቃ | የመቶ ሰው አዛዥ |
| ሻምበል | የኮምፓኒ አለቃ ሁለት መቶ ሀምሳ ለው አዛዥ |
| ሻለቃ | የአንደ ሺ ሰው አዛዥ |

ፊታውራሪ ደግሞ በሰሩ የሶስት ሻለቃ ጦር ይኖረዋል

የማዕረግ እርከኑ ደግሞ ከታች ወደ ላይ ከባሻ፣ ባላምባራስ፣ ግራዝማች፣ ቀኛዝማች፣ ፊታውራሪ፣ ደጃዝማች እና ራስ (ማርሻል) ነው። ማዕረጉ በትክክል የሚያዙትን ሰው ቁጥር ላይገልፅ ይችላል። ምናልባትም ቀደም ሲል የተወሰነ ደንብ ሊኖረው ይችላል አሁን ግን የለውም።

በታህሳስ አምስት በጥዋቱ ደጃዝማች የሠራዊቱ ቁጥር እንዲታወቅ ትዕዛዝ አስተላለፉ። ምልክት በሚሰጥበት ጊዜ ብረት ወይም መሳሪያ መያዝ የሚችል ወንድ ወደ ክፍት ሜዳው ወጥቶ መሰለፍ አለበት። ሁሉም ሰው ድምፁን አጥፍቶ እንዲንቀሳቀስ ታዟል ምክንያቱም ድንገት አውሮፕላን ቢመጣ ከፍታ ቦታ ላይ ሆነው የሚጠብቁ ሰዎች የሚተኩሱቱን የማስጠንቀቂያ ተኩስ መስማት እንዲቻልና ሁሉም ወደ መጠለያ ወይም ጫካ በመግባት መደበቅ እንዲችል ነው። አጋጣሚ ሆኖ ያን ቀን ምንም አውሮፕላን አልመጣም።

ከጥዋቱ ሶስት ሰአት ሲሆን ሰው እንዲሰበሰብ ጥሩምባ ተነፋና ከአንድ ሰአት በኋላ ቆጠራው ተጀመረ። ስድስት ሺ ሰዎች ብቻ በሶስት ረድፍ ተሰልፈው ከሜዳው በአንድ በኩል ቆመዋል። ከዚህ ውጭ በሌላ ቦታ አራት ፊታውራሪዎች ከጦራቸው ጋራ እንዳሉ ታወቀ።

መጀመሪያ የቀኝ ዘበኞች በየኮምፓኒያቸው በመሆን በሁለት ረድፍ ተሰልፈው በደጃዝማች ፊት አለፉ። ተጨማዶ የተሰፋው ዩኒፎርማቸው አላላመራቸውም፤ የሰልፍ መስመራቸውንም አልጠበቁም፤ ነገር ግን ጠንካራ ይመስላሉ። መሳሪያዎቻቸው ደግሞ በደንብ የተያዙ ሲሆን ሁለት ጥምጥም ዝናር ሙሉ ጥይት በትከሻቸው ላይ አድርገዋል። አራቱ ከባድ አውቶማቲክ መሳሪያዎችም በደንብ ተይዘዋል፤ ካርታና የጥይት ሣጥኖች ሳይቀር

በደንብ ተይዘዋል፡፡ የጋማ ከብቶቹ ፈረሶችና አህዮቹም ሳይቀር ያረፉና የወፈሩ ናቸው፡፡ ለሶስት ቀን ስንቅ የሚይዝቡት ከረጢት በስተቀር ወታደሮቹ ሌላ ጓዝ አልያዙም፡፡ አያሌው በነዚህ ወታደሮች እንደሚኮሩ ግልፅ ነበር፡፡ አልፎ አልፎ እኔን ሠረቅ እያደረጉ በማየት ወታደሮቹ ያሳደሩብኝን ስሜት ለማየት ሲሞክሩ አስተውያለሁ፡፡

ከዘቦቹ በኋላ ሌሎች ወታደሮች በየደረጃቸው ተሠልፈው መጡ፡፡ በአንዱ መሰመር ሁለት ሰዎች ብቻ አንድ አይነት ጠመንጃ ይዘዋል፡፡ በግምት ከየመቶው ሰው ሰባቱ ጎራዴ ብቻ ወይም በትር የያዙ ናቸው፡፡ በተለይ የማስታውሰው የአሥራ ስምንት አመት ወጣት ልጅ በኩራት መንፈስ ዱላውን በቀኝ ትከሻው ላይ አድርጎ ይንጎራደድ ነበር፡፡ ዱላው የአንጨት ሲሆን ቀይ ቀለም ያለው ሆኖ አላዩ ላይ ጌጥ ተቀርፆበታል፡፡ የዚህ ወጣት ልጅ የተለየ ኩራትና አካሄድ የሰዎችን አይን የመሳብ ችሎታ ፈጥሯል፡፡

ደጃዝማችም አስጠሩትና

"ዕድሜህ ስንት ነው?"

"አባቴ የሚነግረኝ በንጉሥ ሚካኤልና በሸዋ ገዥዎች መሀከል በተደረገው የሰገሌ ጦርነት ወር ነው የተወለድኩት"

"መልካም በዚህ በሚያምር ዱላህ ምን ልታደርግበት ነው?"

"በዚህ ዱላ ነጭ ልገልበት ነው"

"እንደሱ እንኳን ማድረግ አትችልም በምትኩ ጠመንጃ ልስጥህ"

"የለም አመሰግናለሁ፤ ለአባቴ የማልኩት ቃለ መሀላ ጣልያን ገድዬ ጠመንጃውን ወስጄ አሳያለሁ፤ አለዚያ በዚህ በጦር ሜዳ እቀራለሁ"

ቀጥሎ ደግሞ ጠመንጃና ጥይት ሁሉም ተመልሶ ተሰብስቦ እንደገና በየአይነቱ ተመድቦ ለእያንዳንዱ ወታደር ስም እየተፃፈ የወሰደው ጠመንጃና አይነትና የጥይት ቁጥር እንዲመዘገብ የሚል ትዕዛዝ ተላለፈ፡፡ የማጉረመረም ድምፅ ተለማና በሚከራከሩ ድምፆች ተከተለ፡፡ ሁኔታው አደገኛ መሰለ ነገር ግን ደጃዝማች ለዚህም ተዘጋጅተው ስለነበር ሰዎቹን ማረጋጋቱን አወቅውበታል፡፡ ወድያውኑ ይህንን ትዕዛዝ መስጠት የተገደዱት በቂ ምክንያት ስላላቸው ነው፤ በምትኩ ግን እያንዳንዱ ወታደር ከጠላት የወሰደውን ጠመንጃና ጥይት የራሱ ማድረግ እንዲችል ተፈቅዶለታል አሉ፡፡ የደሰታ ጩኸት ከመላው ሠራዊቱ ተሰማ፤ ተከትሎም መዝጋቢዎቹ ከሚችሉት በላይ እስኪሆን ድረስ በፈቃደኛነት መሳሪየዎች በፍጥነት መመለስ ጀመሩ፡፡



በአቢሲኒያ ከጥንት ጀምሮ በጦርነት ምርኮ የተገኙ ዕቃዎች በሙሉ ለተዋጊ ወይም ለማራኪው ነው የሚሆኑት፤ ሆኖም መሣሪያና ጥይት ግን ጦርነቱ እንዳበቃ ያለምንም ሽልማት ለመንግሥት መመለስ አለባቸው፡፡

የመጨረሻው ወታደር ተመዝግቦ እንደጨረሰ ጦሩ እንደገና ተጠራ፡፡ እያንዳንዱ የሻምበል ጦር አንድ አይነት ጠመንጃ ለእያንድዳንዱ ሰው ከመቶ ጥይቶች ጋር እንዲሰጥ ተደረገ፡፡ ጠመንጃ ያልደረሳቸው ሰዎች ለደህንነታቸው ሲባል ጠመንጃ ከያዙት ጋር እንዲመደቡ ሆነ፡፡ ይህም ከጠላት የተማረከ ጠመንጃ እስከሚያገኙ ድረስ ወይም ጠመንጃ የያዘ ሰው ሲሞት የሚቹን ጠመንጃ እስኪወስዱ ድረስ ነው፡፡

ይህንን እለላለፍ ማየት የሚገርም ነበር ቀኑም በፍጥነት ወደ ምሽት ተቃረበ ልክ ከምሽቱ 12 ሰአት ሲሆን ሁሉም ነገር ተከናወነና ወደ ካምፓችን ተመለስን፡፡

ዘግየት ብሎ ማምሻውን ለሌሎች ጦር አዛዦች በተመሳሳይ አይነት ሥርአት ጠመንጃና ጥይት እንደገና እንዲከፋፈል እንዲያደርጉ ትዕዛዝ ተላለፈ፡፡

ማታውኑ ደግሞ ወደ ራስ እምሩ የተላከው መልከተኛ ተመልሶ መጣ፡፡ የራስ እምሩ የጎጃም ጦር ዳባትን ለቆ በሊማልሞ በኩል አድርጎ ወደ ሽሬ እየተጓዘ መሆኑን ተናገረ፡፡ እንግዳ የሆነ ነገር፡፡

በዚህ ዜና ምክንያት ደጃዝማች ካምፑን ለመልቀቅ ወሰኑ፡፡ በሌሊት ተነስተን ከፍታው 500 ሜትር ከሚሆን ከራስ ኮረብታዎች ግርጌ ለመስፈር ነው የተወሰነው፡፡ ርቀቱ ወደ አስር ኪሎሜትር ይሆናል፡፡ ዝቅ ያለው ቆላማ ቦታና ወይም ደረቁ መሬት ጫካ ለላልነበረው ድንኳን እንዳይተከል ትዕዛዝ ተላለፈ፡፡ ደጃዝማችም ቢሆን ከአንድ ድንኳን በስተቀር ሌሎች ድንኳኖቻቸውን ትተው ነው የመጡት፡፡ ጦሩ ዝቅ ያሉ ቁጥቋጦዎችን ለመኝታ ለመደበቂያ ወይም ለመከላከያ እንዲጠቀም ስለታዘዘ ከበድ ያለ ወይም የተንዛዛ ጓዝ እንዲቀር ተደረገ፡፡

ወደ ሁለት ሺ የሚሆኑ እያንዳንዳቸው ሁለት ሊትር የሚሆን ውሀ መያዝ የሚችሉ ከረጢቶች ብዙ ዕቃ ላልተሸከሙ ሰዎች እንዲሠጡ ሆነ፡፡ ውሀ የትኛው ቦታ ሊኖር እንደሚችል ማንም ለው መገመት አይችልም፤ ስለዚህ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ከረጢቶች በውሀ መሞላት አለባቸው፡፡

እንግዲህ አንድ ነገር እንደሚሆን እያወቅን መጣን፡፡

ወታደሮች የሚይዙትን ነገር ማዘጋጀት፤ መሳሪያቸውን መወልወል፤ ጎራዴያቸውን መሳል ጀመሩ። የጦርነት ቀረርቶና ፉከራ ተጀመረ። ከዚህ በፊት ጦር ሜዳ የዋሉ ለአዲሶቹ ታሪካቸውን መንገርና መፎከር ተጀመረ። ጀግናው መሳሪያውን ጨብጦ ወደ ፊትና ወደኋላ እየተንጎራደደ ስላደረገው ጀግንነት ፉከራ ያሰማል። በመሀል ወደ ፊት ይገሰግስና እዳማጩ ፊት ጉራዴውን መዞ እንዴት ጠላቱን እንደሚያጠቃ ያሳያል። ላልተዘጋጀ ሰው አደገኛ ነው። በእንደዚህ አይነት ትዕይንት ብዙ የአውሮፓ ሰዎች በድንጋጤ እመድ ሲመስሉ አይቻለሁ። ነገሩ ግን ከፋት የሌለው ነገር ነው። እንዲህ አይነቱ እንቅስቃሴ በአገሬው ሰዎች በጣም ነው የሚከበረው።

በጣም የዳጉት ሰዎች መንቀሳቀስ ከሚገባን ሰአት ቀደም ብለው ጉዞ ጀምረዋል። ረጅም የማያቋርጥ የሰዎች መስመር ከካምፑ እየለቀቀ ሲሄድ ይታያል። ሰዎቹን ማሰቆምም አልተቻለም።

ከካምፑ መልቀቅ ስንጀምር ከደቡብ አቅጣጫ አንድ አውሮፕላን መጣ፤ በሚገርም ሁኔታም እኛን ሳያየን ወደ ሰሜን አቅጣጫ መንገዱን ቀጠለ። እየመሸ ከቀኑ አሥራ አንድ ሰኣት ስለነበር በዚያን ቀን የመጣው አውሮፕላን አንድ ብቻ ነበር።

የቁልቁለቱ መንገድ ካሰብነው በላይ አስቸጋሪ ነበር። የከብት መተላለፊያ መንገድ ሆኖ ቁልቁል ሰለት ወዳላቸው የአለት ድንጋዮች ነው የሚወስደው። በአንድ ቦታ መንገዱ የሚያዳልጥ ዳገትነት ባለው የአለት ንጣፍ ላይ ነው የሚያልፈው። ከስር የሞቱ ፈረሶችና አህዮች ይታያሉ። አለቱ ላይ ቆንጥጠው መርገጥ ስላልቻሉ ተንከባለው ወድቀዋል። እዚህ ቦታ ላይ ሁሉም የጭነት ከብቶች ጭነታቸው መውረድ ነበረበት።

አልፎ አልፎ የድንጋይ ናዳዎች ከላይ ወደታች ይወርዳሉ። ከዳጃዝማቹ ጎን ለጎን እየሄድኩ ግማሽ መንገድ የሚሆን እንደሄድን ድንገት ከላይ በኩል ጨኸት መሰማት ጀመረ። ለማሰብም ጊዜ አልነበረንም፤ የሰዎች እጆች ሁለታችንም ጎትተው ወደ አለቱ ግድግዳ ወረወሩን። እዛው ላይ ተደግፈን ቁጭ እንዳልን በላያችን ላይ እንደጉም ጥላ አለፈ። ድንጋይ ናዳ ከነአቧራው ነበር። ከስር ናዳው መሬት ላይ ሲወርድና ሲንከባለል መሰማት ይቻል ነበር። ከናዳው ጋር አብሮ የወረደው ከላይ ከከፍታው የተንከባለለ የጭነት ፈረስ ነበር። ንቁ ዘቦች ተፈናጥረው ባይወረውሩን ኖሮ እኛ ላይ አርፎ ይጨፈልቀን ነበር።

ከብዙ ችግር በኋላ ከምሽቱ ሶስት ሰአት ሲሆን ካምፕ የምናደርግበት



ቦታ ደረስን። አዲስ ነገርም ነው የጠበቀን። ሰው ያልነካው ቦታ ነበር። ሳሩ ራሱ ከሰው ቁመት በላይ አድጓል ግን እንደ ማገዶ እንጨት ድርቅ ያለ ነው። አንድ ግድ የለሽ የሆነ ሰው በጀመረው እሳት ሳሩ መንደድ ጀመረ። በቅፅበት ቁመት ያላቸው የእሳት ነበልባሎች በከፍተኛ ድምፅ ወደ ፊት እየተቀጣጠሉ ሲወረወሩ ማየት ጀመርን። እራሳችን በዚህ ሣር ሜዳ መሃል ላይ ነው የነበርነው። ተመስገን ነፋሰም አልነበረምና በመቶ የሚቆጠሩ ወታደሮች ተረባርበው እሳቱን ባያጠፉት ኖሮ ብዙዎቻችን በዚሁ እሳት ተቃጥለን እንሞት ነበር። ይህ ሁሉ የሆነው በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ነበር።

አባቦች ደግሞ ሌላ ችግር ፈጥረውብን ነበር። ያን ቀን ማታ የተገደሉት አባቦችን ቁጥር ሳይ መሬቱ በሙሉ እንዳለ በአባብ የተሞላ ነው ያሰብላል። በየቦታው አባብ በዱላ ሲቀጠቀጥ ከዚያ ቀጥሎ በአፎይታ "እንካ ቅመሰ የታባክንሰና" የሚል ድምፅ እንሰማለን።

ከአንዲት ሴት በስተቀር በአባብ የተነደፈ ሰው አልነበረም።

እንደ አባብ ፈርሃቱ ምንም እንቅልፍ ሳይዘኝ ነው ያደርኩት፤ ሆኖም ሙሉ ጨረቃ ራሱም ተጨምሮ ነው። ሙሉ ጨረቃ ሲሆን መንገድ ላይ ከሆንኩ እንቅልፍ ነሰቶ ቅዠት የሚለቅብኝ ነገር አለ። በቀን ደግሞ በሙቀቱ ምክንያት ምንም ዕረፍት ማግኘትም አልቻልኩም።

በምሳ ሰአት ደጃች አያሌው ከአንድ ጣልያኖችን ከሰለለ ከኛ ሰው አዲስ መረጃ እንዳገኙ ነገሩኝ። በእንዳባጉና ሰፍሮ የነበረው በሜጀር ከሪኒቲ የሚመራ ጦር ከጥቂት ቀናት በኋላ ካምፑን ለቆ እንደሚሄድ ነው። ሰውየው የጣልያኖቹ ወታደሮች ወደኋላ ይሸሹ ወይም ወደ ፊት ወደ ተከዜ ወንዝ ይንቀሳቀሱ ያወቀው ነገር የለም።

ደጃዝማች ወድያውኑ ወደ ጦር ግንባር መሄድ እንዳለብን ወሰኑ። የሶስት ቀን ስንቅ ብቻ እንዲያዝና ወታደሮች ብቻ እንዲንቀሳቀሱ፤ የምንነሳበት ሰአትም ከቀኑ አሰር ሰአት ላይ እንዲሆን ሆነ። ሌሎቹ ተከታዮችና ጓዝ የሚያጓጉዙት ከኛ በኋላ በጥንቃቄ በአንድ መኮንን ትዕዛዝ እንዲከተሉ ተወሰነ።

ቀጥሎ የተደረገው ጉዞ ግን ከዚህ በፊት አይቼው የማላውቀው ወደፊትም የማልመኘው አይነት ነበር። ደጃዝማችም የመነሳሳት ሰሜት ይታይባቸዋል። በቅሏቸውም ቢሆን የመቁነጥነጥ ሁኔታ ታሳይ ነበር። ሰለዚህ እንደፈለገች እንድትጋልብ ለቀቅ አደረጓት። እኛ ሁላችን መከተል ነበረብን። አህዮችም እየጋለቡ ተከተሏት፤ ወታደሮቹ በሶምሶማ ወይ በሩጫ ይከተሉ ነበር፤ ይህ ሁሉ እንደ ቁንጥንጧ የአዛገዞ በቅሎ ፍጥነት ነበር።

አሰከ ምሽቱ አንድ ሰአት ጉዞው በዚህ ፍጥነት ተካሄደ:: መሀል ላይ የጥቂት ደቂቃዎች እረፍት ነበር ያደረግነው:: መጨለም ሲጀምር ሰላሳ ኪሎሜትር የሚሆን መንገድ ከኋላችን ጥለን መተናል፤ ጨረቃዋ ሙሉ በሙሉ እስከትወጣ መጠበቅ ነበረብን::

የደረስንበት ቦታ ነፃ የወጡ የቀድሞ አገልጋዮች ሠፈር ነበር:: ድንኳን ወጥረው ጠበቁን:: ጠላና ቡናም ተጋበዝን፤ በጣም ጥሩም ነበር:: እነዚህ ነፃ የወጡ አገልጋዮች በደንብ ተደራጅተው ማየት አስገራሚ ነበር:: የራሳቸው አለቃ መርጠዋል፤ የራሳቸው ቤተክርስቲያንና ቄስም ነበራቸው:: በአብዛኛው ወደ ደጋው እየወሰዱ በሚሸጡት በጥጥ እርሻ ነው የሚተዳደሩት:: ቦታውም ለም ነበር:: በሰው ተይዞም ስለማያውቅ የመሬት ባለቤትነት ክርክርም አልነበረም:: ዋናው ጠላት ወባ ነበር:: በያመቱ ብዙ ልጆች ይሞታሉ እንደዛም ሆኖ ቁጥራቸው በመቶዎች የሚቆጠር ደርሷል::

ከሁለት ሰአታት እረፍት በኋላ ጉዞ አንደገና ተጀመረ:: አሁን ግን ረጋ ያለ አካሄድ ነው የምንሄደው:: ሰውም እንሰሳውም በጉዞው ምክንያት ተወጥሮና ደክሞም ነበር፤ የጭነት ከብቱና አውቶማቲክ መሳሪያ የተሸከሙ ወታደሮችን ጨምሮ:: ከዚህ በተጨማሪ ብዙ ወታደሮች እግራቸው ውሀ መቋጠር ጀምሮ ነበር:: በሾህ የተወጋውም በዚያው ልክ ነበር:: መንገዱ ድንጋይ የበዛበትና ዳገት ነበር፤ የነበረው ብርሃን ደግሞ የጨረቃዋ ብቻ ነበር::

የደከሙ ወታደሮች እንሰሳቱም ጉልበታቸው እስኪመለስ ረዘም ያሉ የእረፍት ጊዜዎች መውሰድ ነበረብን:: እንደዚሁ ተጉዘንም መጨረሻ ዛሬማ የሚባል ወንዝ አጠገብ ሰንደርስ አቆምን:: ከሌሊቱ አስር ሰአት ነበር፤ የጥዋት ኮከቦች መውጣትም ጀምረው ነበር:: ባጠቃላይ ወደ ሃምሳ ኪሎሜትር የሚሆን ተጉዘናል::

ማረፍና አቧራና ላባችን መታጠብ ጥሩ ስሜት ነው የፈጠረልን:: ከዚህ ጋር ደግሞ ቡና መጠጣት ብርታት ጨመረልን:: ከዚህ በኋላ እያንዳንዱ ሰው ለመኝታ የሚሆን ቁጥቋጦ ወይ ዋሻ ፈልጎ ማግኘት ነበረበት::

ፊታውራሪ ዘውዱና ፊታውራሪ ሙላው እንዲጠብቁን የተባለው ቦታ ስላልደረሱ ዕቅዱ ተቀየረ ይህም የሆነው ባልታሰበው ብዙ ሰው ባደከመው የፍጥነት ጉዞ ምክንያት ነው:: የደጃማቹን ትግሰት ማጠር ስሜት ለማሟላት ካልሆነ በስተቀር መንገዱ የጠቀመው ነገር ያለ አልመሰለም:: ምናልባትም ይህን የጉልበት ፍተሻ እንቅስቃሴ ያደረጉበት በቂ ምክንያት ይኖራቸው ይሆናል:: ማን ያውቃልስ በድንገተኛ ጊዜ የጦሩን ችሎታ ለማወቅ በዚህ መንገድ ወስነውስ ከሆነ::



# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ጦር ግንባር ደረስን

በነጋታው በአቶ ማሞ ከእንቅልፌ ሰቀሰቀሰ ፀሀይዋ ወጥታ ሰማዩ ላይ ከፍ ብላ ነበር:: ጀርባው ላይ ትልቅ የአሳ ማጥመጃ መረብ ተሸክሟል:: አኔንም አሳ ለማጥመድ ወደ ወንዝ ተከትየው እንድሄድ ጠየቀኝ:: አሳ ማጥመድ አስደለቶኝም አያውቅም ነበር ለማንኛውም አብሬው ሄድኩ፤ የሚያዝናናም ሆኖ አገኘሁት::

የወንዙ ውሀ ከሚወርድበት ግርጌ ቦታ መረጥን:: ውሀው የጠራ ነበር ብዙ አሳዎች ነበረው:: ከትንሽ ሙከራዎች በኋላ እያንዳንዳቸው ሁለት ኪሎ የሚሆኑ ሰምንት ትልልቅ አሳዎችና ብዙ ትንንሾች ጨምረን ያዝን:: ካጠመድናቸው አሳዎች ግማሹን ለደጃዝማች ላክን፤ የተረፉት ደግሞ ወደ አቶ ማሞ መጥበሻ ተወሰዱ::

በዛው ጊዜ ውሰጥ በቀዘቃዛው የወንዝ ውሀ ሰውነታችን በደንብ ታጥበን በትኩሱ በሰሎ የደረሰውን አሳ በላን:: የሚጣፍጥ ነበር::

በዛሬማ ወንዝ ብዙ ጉማሬ እንዳለ ሰምተን ነበር:: በወንዙ ዳርቻ ብዙ የጉማሬ ኮቴ በማየታችን መኖራቸውን አረጋገጥን:: ነገር ግን ሙሉ ቀን ሰንፈልግ ብንውል ደግሞ ጉማሬዎችን ማግኘት ሰላልቻልን ፍለጋውን አቆምን:: እንሰሶቹ ብዛት ያለው የሰው ቁጥር ሲያዩ ሸሽተው ሳይሄዱ አልቀሩም:: የጉማሬው መንጋ ገና በጠዋቱ ያየን ይመስላል::

አመሻሹ ላይ ፊታውራሪ ዘውዱና ሙላው ከወታደሮቻቸው ጋራ ደረሱ:: ካምፓቸውን የአንድ ሰአት መንገድ ርቀው የዛሬማ ወንዝ ገባር የሆነች ትንሽ ወንዝ አጠገብ አደረጉ:: በሚቀጥለው ቀን ደጃዝማች የጦራቸውን አሰላለፍ ግምገማ በሚያደርጉበት ጊዜ አብሮ የመሄድ አጋጣሚ አገኘሁ::

የሁለቱን ሠራዊት አሰላለፍ ማየት የሚገርም ነገር ነበር:: የሁለቱም ሰዎች ወታደሮች ጎን ለጎን ቆመዋል:: የፊታውራሪ ሙላው ወታደሮች የቆላ ሰዎች ሰለሆኑ በለውነት መጠናቸው አነስ ያሉ ናቸው:: ቀጠን ደረቅ ያሉ ሆነው ግን

ንቁና ቅብጥብጥ ናቸው፡፡ የፊታውራሪ ዘውዱ ወታደሮች ደገኞች ናቸው፡፡ ሁሉም በቁመት ከአማካኝ በላይ ረዘም ያሉ ናቸው፡፡ ሰውነታቸው
ፈርጠም ያለ ሆኖ ረጋ ያለ መንፈስ ነው የሚያንፀባርቁት፡፡ ከነዚህ ሁለት አይነት ሰዎች የትኛው በጀግንነትና በድፍረት ጦረነት ላይ ውጤት እንደሚያመጣ በቀላሉ ማወቅ አይቻልም፡፡

እኔን ሲያዩ የሚያሳዩት ባህሪና አመለካከታቸው አላስደሰተኝም፡፡ ደጃዝማች አየቀለዱ የመጀመሪያው የነጭ ምርኮኛ ይኸውና ሲሉ ያሳዩት ሁኔታ በተጨማሪ ጥሩ አልነበረም፡፡ በእኔ ጥያቄ ደጃዝማች በኋላ እኔ ማን እንደሆንኩ ከነሱ ጋራም ምን እያደረግሁ እንደሆነ ማብራሪያ ሰጡ፡፡

ማምሻውኑ ካምፑን ለቀን ሰሙን የረሳሁት ትንሽ ወንዝ አጠገብ ሌሊቱን አላለፍን፡፡ የማሊታውሰው ነገር ቢኖር አንድ ወታደር ዘንዶ መግደሉን ነው፡፡ ሰውየው ከአንድ ዛፍ ስር ተጋድሞ ነበር፡፡ በጥዋት ሲነጋ ከላይ የዛፉ ቅርንጫፍ ትልቅ የተጠመጠመ ነገር ያያል፡፡ ተነስቶ ምን እንደሆነ ለማወቅ ጠጋ ብሎ ሲያይ የተጠመጠመው ነገር መንቀሳቀስ ይጀምራል፡፡ ሰውየው ወዲያው ገባውና ከመቅፀበት ጠመንጃውን አንስቶ ዘንዶው ላይ ካርታውን እንዳለ ጨረሰበት፡፡

የሞተው ዘንዶ ቁመት ሲለካ ሰባት ሜትር ነበር፡፡ በግንድ ላይ አንጠልጥሎ ዘንዶውን ወደ ደጃዝማች ለመውሰድ ስድስት ሰዎች መሸከም ነበረባቸው፡፡ የቀኑ ጀግና የተኮሰው ጥይት መጠን ተተከቶለት የሃምሳ ብር ሽልማት ተሠጠው፡፡ በተጨማሪም ጥሩ ንግድ ቀናው፡፡ የዘንዶውን የጎን አጥንት በአስር ብር ሸጠ፡፡ ይህ አጥንት መድሃኒትነት አለው ስለሚባል በጣም ተፈላጊ ነበር፡፡ ከመድሃኒትነት በተጨማሪ ደግሞ ለአስማት ይሆናል፤ ፍቅር ያስይዛል ተብሎም ይታመናል፡፡

ማታውኑ ጨረቃዋ ብርሃን መስጠት ስትጀምር መንቀሳቀስ ጀመርን፡፡

በዛሬማና በዱኮኮ ወንዝ መሀል ያለው መሬት የሚቀጥለው ካምፕ ቦታችን ነው፡፡ ይህ ቦታ በአቢሲኒያ ስመጥር የሆነው የዋልድባ ገዳም ቦታ ነው፡፡ መሬቱ ቅዱስ ነው ስለሚባል ለአርሻ አይጠቀሙበትም፡፡ ለው የማይነካው መሬት ስለሆነ የተለየ አንግዳ የሆነ የዛፍ አይነት በብዛት ያድግበታል፡፡ ይህ ዛፍ ቅጠል የማይኖረው ጊዜ አለ፤ ግንዱም አንደ አገዳነት ይቃጣዋል፡፡ በጣም በፍጥነት ስለሚያድግ አንጨቱ ለስላሳ ይሆንና ከእንጨት ይልቅ ወረቀት ይመስላል፡፡



ገዳሙ በአንድ ትንሽ ወራጅ ውሀ ከሁለት ቦታ ተከፍሏል፡፡ በአንድ በኩል ቤተክርስቲያኑና መኖሪያ ቤቶች ያሉበት ነው፡፡ ተራ መነኩሴዎችና ዲያቆናቱ በዚህ ቦታ ይኖራሉ፡፡

በሌላው በኩል ግን ማንም አንግዳ አንዲገባ የማይፈቀድለት ቦታ ነው፡፡ በዚህኛው ቦታ የሚኖሩት ደግሞ የበቁ መነኩሴዎች ወይም መናኞች ናቸው፡፡ እነዚህ መነኩሴዎች ወይም መናኞች ለአንድ አመት ከሰው ተለይተው የጫካ ሥራስርና ቅጠል እየበሉ ለመኖር መሀላ የገቡ ናቸው፡፡ አንድ አመት ሲያልፋቸው ወደ መኖሪያው ቦታ ይመለሱና በቦታቸው ደግሞ ሌሎች መናኞች ይተካሉ፡፡

ለዋልድባ አካባቢ የተቀደሰ መሆን ሁለት ምክንያቾ አሉት ይባላል፡፡ አንደኛው ምክንያት አዳኛችን (ኢየሱሰ ክርስቶሰ) በምድር በነበረበት ጊዜ ይህን ቦታ በእግሩ ተራምዶበታል፡፡ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ በክርሰትና ሀይማኖት መጀመሪያ አካባቢ 999 ቅዱሳን ከሮማ ተነስተው ወደዚህ መጥተዋል ነው፡፡ የመጡበት ምክንያት ደግሞ በዚህ ሰፍራ በሰላም ለመሞት ነው፡፡ ስለዚህ እነሱ በተቀበሩበት በዚህ ቦታ የቀረው የቅዱሳኑ አፅም መረበሽ የለበትም፡፡

የዋልድባ ገዳም አከብሮት ሀይል በግልፅ መታየት የሚችል ነገር ነበር፡፡ ሁሉም ወታደሮች ቦታውን በእምነትና በአከብሮት ስለሚያዩት ሲነጋገሩ እንኳን እየተንሾካሾኩ ነበር፡፡

አኩለ ሌሊት ሲሆን ብጫ ቀሚስ የለበሱ መነኮሳትና ዲያቆናት በሰልፍ ተቀበሉን፡፡ መምጣታችን ስለሰሙ አቀባበል አደረጉልን፤ ምግብና ጠላ ቀረበልን፡፡ የፍራፍሬ ከምሮች አንደ ሙዝ፣ ብርቱካን፣ ሎሚ፣ ፕላም እየተዘረ ለሰው ተሠጠ ተጋባዦችም በደስታ ተቀበሉት፡፡ ለረዥም ጊዜ አንደዚህ የመሰለ ነገር ያየ ለው አልነበረም፡፡ የገዳሙ ትልቅና በደንብ የተያዘ የፍራፍሬ ተክል እርሻ አለ ተብሎ የሚወራውን ወሬም አረጋገጠልን፡፡

የገዳሙ ህላፊ አባ ገብረ ሥላሤ መጥተው ተገናኘን፡፡ አባ ገብረ ሥላሴ ሶስት መቶ የሆኑ የታጠቁ ወታደሮቻቸውን ይዘው ጦር ሜዳ ሲከተሉን ነው፡፡ የቤተክርሰቲያን ሰው ስለሆኑ ጠመንጃ መያዝ አይችሉም ነገር ግን በሁለት ጎኑ ስለት ያለው ጎራዴ ከኮርቻቸው ላይ ተንጠልጥሎ ይታይ ነበር፡፡

ከሌሊቱ ሰምንት ሰአት ሲሆን ደቀቆ የሚባል ወንዝ ለንደርስ ፊታውራሪ ሽፈራው ከቦታው ሲጠብቁን አገኘናቸው፡፡ ምንም ሌሊት ቢሆንም

የፊታውራሪው ወታደሮች ነቅተው ሲጠብቁን ስለነበረ በፉከራና በሽለላ ነው የተቀበሉን፡፡ እንዳበደ ሰው ወዲያ ወዲህ እያሉ የሚያቅራሩትና የሚፎክሩ ሰዎች ከዚህ በፊት አይቸው የማላውቀው አይነት ነበር፡፡ ዋነኛው የጦርነት ስሜት መታየት ጀምሮእል ለእኔ ግን የበዛና የተጋነነ መሰለኝ፡፡

በሚቀጥለው ቀን እዲስ የተቀሳቀሰን ጦር እሰሳሰፍ ግምገማ ተደረገ፡፡ ግምገማው በኢጣልያ ቃኝ ወይም ሰላይ እውሮፕላኖች ምክንያት ሁለት ጊዜ መቋረጥ ነበረበት፡፡ በዚህ ሁኔታ እያለን እንዳባጉና ያለው የኢጣልያ ሜጀር ወደኋላ እንዲያፈገፍግ ትዕዛዝ የተሠጠው መሆኑን ሰማን፡፡ ምክንያቱም የነበረበት ቦታ ቀደም ያለ ወይም ገባ ያለና አደጋ ያለበት ነው ተብሎ ነው፡፡

ውይይት ተደረገና ውሳኔው የሚሸሸውን የኢጣልያ ወታደር ለመዝጋት ምሽጉን ከበን እንድንይዝ ሆነ፡፡

ምሽቱ ሳይ የሶስት ፊታውራሪ ጦር ተሻገር፣ ሙላው ና ዘውዱ ወደኋላ ተመልሰው ተከዜ ወንዝን በማቋረጥ በምሽጉ ምዕራብ በኩል እንዲከቡ ታዘዙ፡፡ ያም የሌሊት መንገድ ነው፡፡ ፊታውራሪ ሽፈራው ደግሞ የራሳቸውን 2500 ወታደሮች ይዘው አንድ ሺ ወታደር ተጨምሮላቸው በምሥራቅ በኩል ተንቀሳቅሰው ሐይዳን አቋርጠው ማይ ጥምቀት በመሆን ትዕዛዝ እንዲጠብቁ ተወሰነ፡፡

የጦርነት እንቅስቃሴው ተጀምሯል፡፡ ደጃዝማች በሚሠጡት ትዕዛዝ የረኩ ይመስላል፡፡ በኋላ እንደነገሩኝ ከሆነ በዚህ በጣም ደስተኛ እንደነበሩ ነው፡፡ "ጠላት ላይ ጥቃት ለማድረስ የመጀመሪያው ስለሆንኩ ሸዋ ላሉት ገዥዎች የማልፈራ መሆኔን እስመሰከራሁ" ቀጥለውም " አገራችን አደጋ ላይ ባለችበት በአሁኑ ጊዜ የአንድ ሰው ምኞትና ፍላጎት ምን ሚና አለው? ንጉሡ እንደኛ ሰው ናቸው፤ አቢሲኒያ ግን የሁላችንም እናት ነች፡፡"

በሚቀጥለው ቀን ታህሳስ አምስት ከራስ እምሩ የተላከ ደብዳቤ ይደርሳል፡፡ በደብዳቤው መሰረት ራስ አምሩ አዳርቃይ እንደሚገኙ ይህም የተሠጣቸው ትዕዛዝ ወደ ሽሬ ግንባር እንዲሄዱ ስለሆነ ነው፡፡ ደብዳቤውም ደጃች አያሌው ወደ እርሳቸው እንዲመጡና ስለ ጦርነቱ አሰሳሰፍ እንዲነጋገሩ ይጠይቃል፡፡ ደጃዝማች ለረዥም ሰአት በማሰብ ከተቀመጡ በኋላ ለመልከተኛው

"ተመሰስና ለጌታህ ዛሬ ማታውን ወደ እሰዎ እመጣለሁ ብለህ ንገር" ብለው ነገሩት፡፡



ወደ አዳርቃይ መንገዱ ወደ ሰላሳ ኪሎሜትር ይሆናል እና ራስ እምሩ እንዲህ ያለ የማይመች ነገር ለምን እንደጠየቁ ማሰብ ጀመርን፡፡ ነገሩ በጣም አስቸኳይ ከሆነ ለምን ግማሽ መንገድ መጥተው አንገናኝም?

ሙሉውን ቀን ደጃዝማች አጠር ያሉ ትዕዛዞች ከመስጠት በስተቀር በሀሳብ ተውጠው ነው የዋሉት ፡፡ በታህሳስ ሰባት በጥዋቱ ተነስተው ሰመሄድ እቅድ አድርገዋል፡፡ ሶስት መቶ የሚሆኑ የራሳቸውን ዘቦች ይዘው ሰመሄድ የቀረው ጦር ግን በፊታውራሪ ተሻገር መሪነት ወደ ሀይዳ እንዲሻገር ተወሰነ፡፡ ፊታውራሪ ሽፈራው ደግሞ ሌሊቱን ወደ እንዳባጉና እንዲገሰግሱ ተመከረ፡፡

ደጃዝማች መንገዳቸውን ፀሀይ ገና ሳትጠልቅ ጀመሩ ሆኖም ጨረቃዋ እስክትወጣ ድረስ መጠበቅ ነበረብን፡፡ መንገዱ በወንዞችና በገደሎች መሀል ስለሆነ አስቸጋሪ ነበረ፡፡ ጉዟችንም አዘገየብን፡፡ ቋጥኞችና የዋርካ ዛፎች በጨረቃው ብርሃን መሬቱን የተለየ መልክና አቀማመጥ ሰጥተውታል፡፡

የዋርካ ዛፍ ትንንሽ ቅጠሎች ያሉት ሲሆን ሙሉ በሙሉ ሲያድግ ከሰምንት እስከ አስር ሜትር ከፍታ በላይ ይሆናል፤ የጎን ስፋቱም ከሁለት እስከ ሶስት ሜትር ነው፤ የግንዱ ወይም የልጡ መልክ የድንጋይ መልክ ያለው ነው፡፡ ዛፉ ሲያረጅ ከብዙ መቶ አመታት በኋላ ግንዱ ከውስጥ መበስበስ ይጀምርና ወደላይ ወደ ቅርንጫፎቹ ይሄዳል፡፡ በነዚህ በበሰበሱ ግንዶች መሃል የዝናብ ውሀ ስለሚቋት በደረቅ ቦታ የሚኖሩት የሀገሬው ሰዎች ውሃ ይቀዱበታል፡፡

ከአቶ ማሞና ባለቤቱ ጋራ ጎን ለጎን እየጋለብን ከኋላችን ደግሞ የጭነት ከብትና አገልጋዮችን አስከትለን እየሄድን ነበር፡፡ በሁለት የወታደር ምድቦች መሀከል ባለው ክፍተት ስለምንጓዝ ብቻችን ነበርን፡፡ አገልጋዮቻችን እርስ በራሳቸው ታሪክና ቀልድ እያወሩ ይጓዙ ነበር፡፡ በአቢሲኒያ ያለፈ ታሪክ እያወሩ ጊዜ ማሳለፍ ከሚወደድና ከሚከበሩ ነገሮች አንዱ ነው፡፡ በወሬያቸው መሀከል ይስቁ ስለነበር የመረጋጋት ምልክት ነበር እኛም ቢሆን ጨዋታውን ማዳመጥና አብረን መሳቅ ጀመርን፡፡

ምናልባት የአንድ ሰአት መንገድ የሚሆን እንደተጓዝን መንገዱ ድንገት የያዝነው ጓዝ ማለፍ በማይቻልበት ጥቅጥቅ ባለ ጫካ ተዘግቷል፡፡ አንድ ሰው እንደምንም ብሎ ወደ ጫካው ውስጥ ገብቶ ወዲያውኑ ተመለሰ፡፡ የነገረን ጥሩ ዜናም አልነበረም፡፡ ከጫካው ቀጥሎ ደረቅ ወንዝ ነው እንጂ መንገድ እንደሌለ ነው፡፡ አሽከሮቹን እንዲጣሩ ጠይቀን ቢጣሩ ቢጣሩ መልስ የለም፡፡ እንግዲህ ጠፍተናል ማለት ነው፡፡

ሰማይ ያሉት ከዋከብት ትልቁ ዲፐርና የሰሜን ኮከብን ስናይ መንገዳችን ይዘን ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ከመቀጠል ይልቅ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ገፋ አድርግን ተጉዘናል:: የመንገድ ልምድ ያለን ሰዎች ሁላችንም እንዴት ብለን በግድየለሽነት በመዘንጋት ቆላማው ቦታ እንደገባን ሲገባኝ ያልቻለ ነገር ነው:: ብዙ የእንስሳ ኮቴዎች በየዛፉና በየቁጥቋጦው ስር እዚህም እዚያም ይታያሉ:: ስለዚህ አንድ ሰው ተጠንቅቆ ካላየ በስተቀር ትክክለኛውን መንገድ ሊስት ይችላል::

አሁን ምን ማድረግ እንችላለን? ትክክለኛውን መንገድ ለማግኘት ወደኋላ ብንመለስ ከጦሩ ኋላ መዘግየትና መራቅ ሊመጣ ነው:: ይህ ደግሞ የራሱ አደጋ አለው:: ቀማኞች ብዙ ጊዜ ከጦር ራቅ ብለው በመከተል ጓዝ ይዞ የሚከተለው የጦር ክፍል ለብቻው ሲሆን ማጥቃት ይሞክራሉ::

ስለዚህ ወደ ደቡብ ምሥራቅ አቅጣጫ ብንሄድ ከጦሩ ጋር መገናኘት ወይም ሀይዳ ልንደርስ እንችላለን:: የዚህ ምሽት ግባችን ነው::

ማንኛችንም ቢሆን የተከተለውን እንገት የሚሰብር መንገድ የሚረሳ የለም:: ሽቅብና ቁልቁል፣ በጅረቶች መሀከል፣ በአለቶች መሀከልና በአለቶች ላይ የሚንከባለሉ ድንጋዮችን ጨምሮ በዛፎች ግንዶችና ስሮች መሀከል የተደረገ ጉዞ ነበር:: ከፍና ዝቅ በማለት ከአለት ስንሰለት ጎን እንደምንም ራሳችንና እነዚህን የሚያሳዝኑ እንስሳቶች እየጎተትን በዝግታ ወደፊት መጓዝ ቀጠልን:: ስምንት ጊዜ በጠባብ ቦታ መንገድ በአለቶች መሀከልና ደግሞ እንደ ገደል ቀጥ ባለው የወንዙ ዳርቻ ለማለፍ የእንስሳቶችን ጭነት ማውረድ ነበረብን::

አንድ የጭነት ከብት በተሰይ ቀጥ ብሎ መሄድም አልቻለም ነበር:: በየጊዜው እየወደቀ ተቸግሮ ነበር:: ከመሀከላቸው ጠንከር ብዬ ስለተገኘሁ መደገፍና እንዳንድ ጊዜም ይህንኑ እንስሳ መግፋት ነበረብኝ::

ሶስት ጊዜ አንበሳ ሲያገሳ ሰማን:: አንደኛው ጊዜ እየተቀባበሉ ሲያገሱ ነበር:: ይህንን መስማት የሚያስደንቅ የሚያስደስትም ነበር ነገር ግን ከብቶቻችን ላይ ችግር ፈጠረ:: ከብቶቹ ሁሉንም ነገር ይፈሩ ነበር::

ፀሀይ መውጣት ጀመረች ነገር ግን ወደ ሀይዳ የሚወስደውን መንገድ ማየት አልቻልንም ነበር:: ራብና ጥማት ይሰማን ጀመረ ከሁሉም የሚብሰው ግን የውሀ ጥማቱ ነበር:: ሌሊቱን በሙሉ ስንጓዝ አንድ የውሀ ጠብታ እንኳን አላየንም::



አንድ ጊዜ አውሮፕላን መጥቶ በተደጋጋሚ ከዞረን በኋላ የግድ ሠቢታተንና እንስሶቹን ለቀን ባገኘነው መጠለያ መደበቅ ነበረብን:: ደግነቱ ሠለሶ በመጥፋቱ ደስተኛ ነበርን::

ጉዞውም ቀጠለና ወደ ሁለት ሰአት አካባቢ ከርቀት ብዙ ቤቶች ወዳየንበት አቅጣጫ መሄድ ጀመርን:: የሀይዳ መንደር መሆኑን ስናውቅ ትልቅ ደስታ ነበር የተሰማን:: ደስታችን የጨመረው ነገር ቢኖር ደጃዝማች ከኩተማው ዳርቻ ከአንድ ትልቅ ዛፍ ስር ከወታደሮቻቸው ጋራ ቁጭ ብለው ስናገኛቸው ነው::

ሰላምታየን ሲመልሱ የአሽሙር መልክ ያሳዩ ነበር:: ከራስ እምሩ ጋራ ከመሆን ለምንድንው እዚህ የመጡት? ለማወቅ ባደረብኝ ጉጉት ጥያቄውን ከመጠየቅ አልተቆጠብኩም::

ለጥያቄዬ ምላሽ ወረቀት አውጥተው ሰጡኝና "ይህንን ደብዳቤ ካነበብክ በኋላ በልብህ ቀብረህ ያዘው" አሉኝ:: መልከቱ ገብቶኛል ካነበብኩ በኋላ አጠገብ ያሉ ሰዎች እንዳይሰሙ ምንም አይነት አስተያየት እንዳልሰጥ ነው::

የተፃፈው ደብዳቤ እንዲህ የሚል ነበር

"ይድረሰ ስተከበሩ ደጃች አያሌው:: ጤንነትዎ እንዴት ነው እግዚአብሄር ምስጋና ይግባውና እኔ ደህና ነኝ:: ዛሬ ማታ ወደዚህ ቦታ እንደሚመጡ ሰምቻለሁ:: የወዳጅዎን ምክር መስማት ከፈለጉ ወደዚህ እንዳይመጡ:: *ራስ እምሩ እስዎን እንዲያስሩ ትዕዛዝ ተሠጥቷቸዋል:: ስዚህ ነው ሠራዊትዎን ትተው ለምክክር እንዲመጡ የጠየቅዎት:: ይህንን አውቃስሁ:: ይስሙኝ እንዳይመጡ:: ተፃፈ ታህሳስ አራት ቀን 1928 አመተ ምህረት:: ነ"

የዚህ ደብዳቤ ምንጭ አስተማማኝ ነው:: በኋላ ብቻችን ስንሆን ደጃዝማች ደብዳቤውን የተቀበሉት በሌሊት ከራስ እምሩ ጦር ካምፕ የግማሽ ሰአት መንገድ ሲቀራቸው መሆኑን ነገሩኝ:: ወዲያውኑ ወደኋላ የመመለስ ትዕዛዝ ሰጥተው የጥዋት ብርሃን ሲወጣ ሀይዳ ደረሱ:: ጦሩ ግማሽ ማይል ርቀት ጫካ ውስጥ እንዲቆይ ተደርጓል::

*ራስ እምሩ እንደ አፄ ሀይለ ሥላሴ ከሸዋው ንጉሥ ሳህለ ሥላሴ የዘር ሀረግ አላቸው:: የንጉስ ሳህለ ሥላሴ ልጅ ወይዘሮ ተናኘ ወርቅ የአፄ ኃይለ ሥላሴ አባት የራስ መኮንንና የራስ እምሩ አያት የወይዘሮ እህተ ማርያም እናት ናቸው:: *Haileseassie's War, Anthony Mockler*

አሁዱን ታህሳስ ስድስት ከኢጣልያ አውሮፕላኖች ጋራ ድብብቆሽ መጫወት ጀመርን፡፡ አንድ ነገር እንደሚሆን ገብቶናል፡፡ ከኢጣልያ ጦር ተጠግቶ ያለው የኛው ወገን የፊታውራሪ ሽፈራው ጦር ውጤት ምን ይሆን ብለን ማሰብ ጀመርን፡፡

ያን ቀን ብቻቸውን ከሚጓዙ መንገደኞች በፊታውራሪ ሽፈራውና በጣልያኖች መሀከል ጦርነት እንደተደረገ ሰማን፡፡ እንደወሬው ከሆነ ጣልያኖቹ ተሸንፍው ሸሽተዋል፤ እኛ ግን አስተማማኝ መረጃ ስላልሆነ በጥርጣሬ ነበር የተቀበልነው፡፡

ከፀሃይ ግባት በፊት አንደ መነኩሴ ከሚታመን መረጃ ጋራ ጥሩ ወሬ ይዞ መጣ፡፡ ከፊታውራሪ ሽፈራው አማች ከፊታውራሪ ነጋሽ የተላከ ደብዳቤ ይዟል፡፡ ደብዳቤው ጣልያኖች በሚገባ ድል የተመቱ መሆኑን ይገልፃል፡፡ አስር ታንኮች የተጎዱ ሲሆን የጣልያን አስረኞች መማረካቸውን ብዙ መሳሪያ በአቢሲኒያውያኖች እጅ መውደቁን ይገልፃል፡፡ ደብዳቤው ጨምሮም አንድ አጃቸው ላይ ስለቆሰሉ ፊታውራሪው መፈረም አለመቻላቸውን ያስረዳል፡፡

ጦሩ ስሰልፍ ሲሰበሰብ ደብዳቤው ተነበበ፡፡ ጀሮ የሚቀድ እልልታ ቀለጠ፤ በአውቶማቲክ መሳሪያ ሀምሳ የሚሆኑ ጥይቶች ወደ ሰማይ ተተኮሱ፤ ይህ የመጀመሪያው ድል ስለሆነ የደስታ መግለጫ ምልክት ነው፡፡

በዚያ ቀን ምሽት ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ወደ ተከዜ ጉዞ ቀጠልን፡፡ መንገዱ እንደተለመደው አስቸጋሪ ነበር፡፡ ማታውኑ ከወንዙ ሁለት ኪሎ ሜትር ርቀት ከአንድ ትንሽ ወራጅ ውሀ አጠገብ አደርን፡፡

በሚቀጥለው ጠዋት ነጎድጓድ በመሰለ አስቃቂ ድምፅ ከእንቅልፌ ነቃሁ፡፡ መሬቱም ይርድ ነበር፤ ያለምንም ማወላወል ወደ መሬት ተወረወርኩና እራሴን ሰብስብ እድርጌ በቅሎዎችን ማየት ጀመርኩ፡፡ በቅሎዎቹ ተረብሸው የታሰሩበትን ገመድ መበጠስ ጀመረዋል፡፡

አሥራ ዘጠኝ በምብ ጣይ አውሮፕላኖች በላያችን ላይ ያንዣብባሉ፡፡ ከኛ በፊት ወደ ሀይዳ ሄደው የከተማውን ግማሽ እንዳልሆነ አድርገው ፍርሥራሽ ብቻ አድርገውታል፡፡ አሁን ተከዜ ላይ እያንዣበቡ ነው፡፡ የወንዙን መሻገሪያ እየደበደቡ ነው ደግነቱ በቦታው ማንም አልነበረም፡፡ ከአንድ ሰአት ድብደባ በኋላ ተመልሰው ጠፉ፡፡ እንደገናም ሳንታይ እመለጥን፡፡


ቀን ደግሞ ተመሳሳይ ድምፅ መስማት ጀመርን፡፡ ይኸኛው ግን ራቅ ካለ ቦታ ነበር የሚመጣው፡፡ የራስ እምሩ ጦር ስሁለተኛ ጊዜ ትምህርቱን እያገኘ ነበር፡፡ ያሁኛው ግን በመርዝ ጋዝ ነበር፡፡ ጣልያኖቹ የራስ አምሩ ጦር ተከዜን



እንዳይሻገር ፈልገዋል፡፡ ውጤቱም ከሶስት መቶ በላይ ሰዎች የሞቱና የቆሰሉበት ነው፡፡

ያን ቀን ማታ ተከዜን ስናቋርጥ የታየው ነገር ሰላማዊ ነው፡፡ ጨረቃዋ ገና አልወጣችም የተከዜ ማቋረጫው ሀምሳ ሜትር ስፋትና የአንድ ሜትር ጥልቀት አለው፡፡ በመቶ የሚቆጠሩ ችቦዎች መሻገሪያው ላይ ለብርሃን እንዲሆን በርተዋል፡፡ ወንዙ ውስጥ ያሉ አዞዎችን ለማስፈራራት በወንዙ ዳርቻ ጥይት ይተኮሳል፡፡ ሰውን ከውሀ መስመጥ የሚያድኑ ዋናተኞች ስርአት አስየዘው ጦሩ በሙሉ ያለምንም ችግር በአራት ሰአታት ውስጥ መሻገር ቻለ፡፡

ወደፊት ጉዞ ቀጠልንና ከጠዋቱ አሥራ አንድ ሰአት ሲሆን በታህሳስ ሰምንት ደብረ አባይ ገዳም ደርሰን መጠለያ አገኘን፡፡ ግማሹ ገዳሙ ውስጥ ግማሹ ደግሞ በሶስት ዋሻዎች ውስጥ ነበር፡፡ ጦሩ ከገዳሙ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ግማሽ ማይል ርቀት የሚገኘውን ጫካ አልፎ እንዳይሄድ ጥብቅ ትዕዛዝ ተሠጠ፡፡




P14

*ዐሀፊው የዘገቧቸው ቦታዎች በካርታው ላይ ይታያሉ*
*(1) ከተከዜ መሻገሪያ ማይ ጥምቀት ጀምሮ (2) እንዳባጉና (3) አፍጋጋ (4) ሰለክላካ የራስ እምሩ ጦርና የደጃዝማች አያሌው ጦር የተጓዙበትን አቅጣጫና የተገናኙበትን ቦታ ያሳያል፡፡ (5) ሳይታሰብ ጎንደር ገስግሶ የገባው የጄኔራል ስታራቼ መካናይዝድ ጦር በኡም ሀጀር በኩል መነሻውን ያሳያል*

# ምዕራፍ አስር

## በቦምብ መጠመቅ

ስኛ የተመደበልን ዋሻ ማለትም ለደጃዝማች እና ለአሽከሮቻቸው መውጫው በትልልቅ ዛፎች የተደበቀ ትንሽ ወራጅ ውሀ ያለበት ጎድጎድ ወዳለ ቦታ ነው፡፡ ለጥበቃ ሰንል በችኮላ አንድ ሜትር ቁመት ያለው ግንብ በገደሉ በከፍቱ በኩል ገነባን፡፡ ለአየር መከላከያ ደግሞ በሶስት አግር ብረት ላይ የተጠመዱ ሶስት አውቶማቲክ መሳሪያዎች የተለያዩ ቦታዎች ላይ እንዲቀመጡ ተደረገ፡፡ ለእነዚህ መሳሪያዎች ደግሞ የታወቁ ኢላማ ተኳሾች ሀላፊነቱን እንዲወስዱ ሆነ፡፡

ይህ እንዳለቀ ወደ ቤተከርስቲያኑ አመራን የጠዋት ፀሎትም እየተደረገ ነበር፡፡ ስነፃ አውጭው ለደጃች እያሴው የምስጋና መዝሙርና ፀሎት ተደረገላቸው፡፡

ጉዳሙ በንጉሠ ነገሥቱ ሞግዚትነት ስር ስለነበር ቤተከርስቲያኑ በብዙ ገንዘብ ተሠርቶ አልቋል፡፡ ከብ ሆኖ ከሚገባው በላይ ትልቅ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን የአይሁድ ህግ መሠረት እንደ ሌሎቸ የአቢሲኒያ ቤተከርስቲያኖች ውስጡ ከሶስት ይከፈላል፡፡ ከውጭ ወደ ውስጥ ቅኔ ማህሌት፣ ቅድስትና፣ መቅደስ ናቸው፡፡ አራቱ በሮችና አሥራ ሁለት መስኮቶቹ ደግሞ ከጥድ የተሰሩና ጌጥ የተደረገባቸው ናቸው፡፡ የውስጥ ግድግዳ ሥዕሎች በአቢሲኒያ ደንብ መስረት የተሣሉና በደንብ የተያዙ ናቸው፡፡ ከሀይለኛ ብርሃንና ከአቧራ ለመከላከል በከባድ የከፊይ መጋረጃዎች ተሸፍነዋል፡፡ ጣራው ደግሞ በቀርከሃ አገዳና በጥድ እንጨት ተጠላልፎ የተሰራ ነው ደማቅ ቀለምም ተቀብቷል፡፡ ከላዩ ላይ የሳር ከፍከፍ ከዛ በላይ ደግሞ የቆርቆሮ ጣራ ተደርጎበታል፡፡

ቤተከርስቲያኑን እየዞርን ልናይ የነበረው ዕቅዳችን ድንገት "መጣች" በሚል ድምፅ ተቋረጠ፡፡ ውጭ የነበሩ በሙሉ ወደ ውስጥ ገቡ ከአውቶማቲክ መሳሪያዎቻችን አንዱ መንጣጣት ጀመረ፡፡


"አሃ! እንዴት ያለ ነገር ነው?"



ሰዎቹ፡ አውሮፕላኑ ቀድሞ ካልተኮሰ በስተቀር አስቀድመው እንዳይተኩሱ ጥብቅ ትዕዛዝ ተሠጥቷቸው ነበር፡፡ በችኮላ ለመፎከር ሲሉ ተኩስ ጀምረው አሳልፈው ሠጥተውን ይሆን? እንዳው ሳታየን ቀርታ ይሆን? ጉዳሙ በኛ ምክንያት ቢደበደብ ደግሞ በጣም የሚያሳዝን ነገር ነው፡፡

ሰላዩ አውሮፕላን ለጥቂት ጊዜ ደጋግሞ ዝቅ ብሎ ከበረረ በኋላ ተመልሶ ሄደ፡፡ ፓይለቱ ያየውን ነገር ተመልሶ እንደሚናገር ተጠራጥረንም ስለነበር እኛም በችኮላ ወደ መደበቂያ ቦታችን ሮጥን፡፡

እንደተጠራጠርነውም ሆነ፡፡



የኢታልያ ሰላይ ወይም ቃኚ አውሮፕላን (ላይብራሪ ኦፍ ኮንግረስ)

ሶስት ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች በከፍተኛ ፍጥነት በአናታችን ላይ አለፉ፡፡ ያን ቀን ማከሰኞ ጠዋት ታህሳስ ስምንት ቀን የቦምብ ጥምቀታችን ተቀበልን፡፡

ቀደም ሲል ከርቀት የቦምብ ፍንዳታ መስማት ራሱ በጣም አስቃቂ ነበር፡፡ አሁን ግን በጣም ቅርብ ሲሆን ጠቅላላ ገሃነም ነው፡፡ ፍንዳታው የብርሃን ጨረር እያሳየ ምድሩን አንቀጠቀጠው፡፡ ዛፎች፣ የቦምብ ፍንጣሪዎች፣ ድንጋይ ስባሪዎች በየአቅጣጫው ሲወረወሩ የፉጨት የመሰለ ድምፅ ከተከታተይ ማጉረምረም ጋራ ይሰማል፡፡ ከዚህ ጋር አብሮ መትረየሶች ከላይም ከታችም ሆነው ይንጣጣሉ፡፡

ግድግዳ ይዘን ተጠጋግተን ቁጭ ማለት፤ አለዚያ ወለሉ ላይ ተዘርግቶ መተኛት ነው፡፡ ደቂቃዎች የረዘሙና የማያልፉ መሰሉ፡፡ ፍንጣሪዎቸ ዋሻው ዙሪያ እየተወናጨፉ ይላተማሉ፤ አልፎ አልፎ አንዱ ወደ ውስጥ ይገባል ሆኖም ጉዳት አያደርስም፡፡ ከመቁሰል ወይም ከፍርሃት የተነሳ ከወጣቶቹ በኩል ልብ የሚሰብር ጩኸት ከውጭ በኩል አልፎ አልፎ ይሰማል፡፡

በኋላ በተለያዩ ጊዜዎች እንዳረጋገጥኩት ከሆነ እንዲህ አይነቱ የቦምብ ድብደባ አንግዳ የሆነ የማደንዘዝ ስሜት ይፈጥራል፡፡ አንድ ሰው ምንም ማድረግ የማይችል መሆኑን ካወቀ የሚያደርገው ነገር አይኖርምም አይሞከርምም፡፡ ለሞት ፍራቻ አልነበረኝም፡፡ ነገር ግን መልሶ ወደ ሀሳብ የሚገባው ነገር ቢኖር በእነዚህ ፍንጣሪዎች መቁሰል ነው፡፡ ከመቁሰልና ከመሰቃየት ደግሞ ቀኑ ደርሶ ከሆነ ፈጣን ሞት ስጠኝ ብሎ ሰው ይመኛል ወይም ይፀልያል፡፡

ይህ የእሳት ትዕይንት አንዳጀማመሩ ወዲያው ቆመ፡፡ ሶስቱ አውሮፕላኖች ያላቸውን በሙሉ አራግፈውብን ሄዱ፡፡ ብዙ ስንቅና ጓዝ ከጥቅም ውጭ አደረጉ፡፡ አሁን እንግዲህ ተመልሰው የአያሌውን ጦር ሙሉ በሙሉ ደመሰስን ብለው ሪፖርት ያቀርቡ ይሆናል፡፡

ሰኛ የነበረን ስሜት አውሎ ነፋስ ሲያባራ እንደነበረ ነው፡፡ ለብዙ ደቂቃዎቸ እየራቀ ከሚሄደው የአውሮፕላኖች የሞተር ድምፅ በስተቀር ሁሉም ነገር ፀጥ ያለ ነበር፡፡

በኋላ ግን ሁሉም ነፍስ ዘራ መጀመሪያ ሁሉም ማወቅ የፈለገው ነገር ሁኔታው እንዴት እንደሆነ ዘመድና ጓደኞች እንዴት እንደሆኑ ነው፡፡

የቆሰሉት መምጣት ጀመሩ፤ እኔም ለሁለት ሰአታት ስማስን ሀያ ስድስት ቁስለኞችን መርዳት ችያለሁ፡፡ አንዳንዶቹ በአሰቃቂ ሁኔታ ተበጣጥሰዋል፡፡ አንዱ ለምሳሌ እጁ ከትከሻው ላይ ተገንጥሎ በጥቂት ጅማቶች ብቻ ተይዞ ተንጠልጥሎ ይታያል፡፡ በሌላኛው ከአሥራ ስምንት ያላነሱ የቆሰሉ ቦታዎችና ሶስት ስብራቶች ቆጥሬአለሁ፡፡ ሁለቱም ለመርዳት ምንም ጊዜ ሳይኖረኝ ወዲያው ሞቱ፡፡

የሞቱት ቁጥር አሥራ ሰባት ነበር፡፡ ከነዚህ አንዱ በጣም የሚታወቅና በሁሉም ዘንድ የሚከበር የዘበኞች መኮንን ነበር፡፡ ትልቅ የቦምብ ፍንጣሪ በግራ ደረቱ በኩል አስከትከሻው ድረስ በመዝለቅ ሰውነቱን ቦጭቆታል፡፡ ቆስሎ የወደቀ ጓደኛውን ሊረዳ ሲል ነው የተመታው፡፡

አሥራ አንድ እንሰሶች ሞተዋል፡፡ ወደኋላ ሁለት በጣም የቆሰሉ አህዮችን ተኩሼ ከስቃያቸው ገላገልኳቸው፡፡ ይህ ግን ማጉረምረም ነው የፈጠረው ምክንያቱም ያገሩ ሰዎች ምንም እንስሳት ላይ ጨካኝ ቢሆኑም እንስሳቱ የሆነውን ያህል ቢሰቃዩም በራሳቸው እንዲሞቱ ይተዋቸዋል፡፡

አመሻሹ ላይ አንድ አውሮፕላን መጣና አስር የአሳትና የፈንጂ ቦምቦች ጣለ፡፡ አላማው ቤተክርስቲያኑን ለመደምሰስ ነበር፡፡ ያም ሆኖ



አልተሳካለትም፡፡ ምናልባትም ፓይለቱ በመሳቱ አፍሮ ይሆናል የቀረውን ቦምብ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ኪሎሜትሮች ርቀት ባለ ሜዳ ላይ አራግፎ በፍጥነት ተመለሰ፡፡ የሚሰጠውን ሪፖረት ማወቅ የሚያጓጓ ነበር፡፡

ከዚህ በኋላ የዚህ አይነቱን ሁኔታ በጦርነቱ ጊዜ ደጋግመን ማየት ችለናል፡፡ አውሮፕላን ዛፍ የሌለበት ጠፍ ሜዳ ላይ ቦምቦችን በተከታታይ ሲጥል አናያለን፡፡ ይህ ሲሆን ሰዎች የሚሰጡት አሰተያየት

"ተመልከት! ልዩ አይን ነው ያላት! አሁን አይጥ ወይም እባብ አይታ ይሆናል" ወይም " አሁን ምጥ ይዟት ነው፤ ይህን ሁሉ አንቁላል መሸከም አልቻለችም"

አውሮፕላኖቹ እንደሄዱ የሞቱትን በቤተክርሰቲያኑ መቃብር ቦታ ከቀበርን በኋላ ወደ ጦር ግንባሩ ወደ አንዳባጉና መጓዝ ጀመርን፡፡ ልክ እኩለ ሌሊት እንዳለፈ ጠላት የነበረበት ባዶ ካምፕ ውስጥ መሀል ላይ ያለ ከፍታ ላይ ደረስን፡፡

በደንብ የተሠሩትን ምሽግ መስመሮችና በየቦታው የወደቁትን ቁጥር ስፍር የሌላቸው ባዶ የምግብ ቆርቆሮ ጣሳዎቸ ላየ ሰው እዚህ ቦታ ነጮች እንደነበሩ ግልፅ ነው፡፡ ሶስት በቀርከሀ ቅጠል የተሰሩ ጎጆዎች ቆመው ይታያሉ፡፡ ውስጣቸው ደግሞ ግድግዳቸው በሲኒማ ተዋናይ ኮከቦች ፎቶ ወይም ኢለስትሬትድ ከተባለ መፅሄት የተወሰዱ ፎቶዎች ተለጥፎባቸዋል፡፡

ከፍታው የሚገኘው ወደ አክሱም በሚወስደው መንገድ ባለበት ሜዳማ ቦታ ነው፡፡ የውሃ ነገር አስቸጋሪ ነበር ምክንያቱም በቅርብ ያለው የውሀ ቦታ አንድ ኪሎሜትር ርቆ ነው የሚገኘው፡፡ በዚህ ምክንያት ምሽጉ ከጥቂት ቀናት በላይ ከበባ መቋቋም አይችልም ነበር፡፡

ከከፍታው ወደ ምሥራቅ በኩል የሚገኝ ሸለቆ ካምፕ የምናደርግበት ቦታ ሆኖ ተመረጠ፡፡ እዛ ለመድረስ ግን አግድሞሽ በጦር ሜዳው ደቡብ በኩል አቋርጠን መሄድ ነበረብን፡፡ በየቦታው ሁሉም አይነት ነገር ተበትኖ ይታያል፡፡ ስኳር፣ በርበሬ፣ ዱቄት፣ ጥጥ፣ ሲጋራ የመሳሰሉት፡፡ የነበረኝ የትምባሆ ስንቅ አልቆ ነበር ብዙ ወታደሮች ጠቀም ያለ የትምባሆ መጠን ከሜዳው መሰብሰብ ችለዋል፡፡

በተጨማሪ ተጎድቶ የቆመ ታንክ ለማየት እድሉ አጋጠመን፡፡ ሞገደኛ ልጅ ተጫውቶ ሲጨርስ የወረወረው የአሻንጉሊት መኪና ከምር ይመስላል፡፡ ከሾፌሩ መቀመጫ ስር የነዳጅ መያዣው ፈንድቶ የታንኩ ውስጡ እንዳለ ተቃጥሏል፡፡ በውስጡ የነበሩ ሁለት ሰዎችም አብረው ጋይተዋል፡፡

የቀረው ታንኩ ላይ የሚታየው መሰባበር ግን በወታደሮቹ ነው የተደረገው:: የተሽከርካሪው ከፍሎች፣ ብሎኖች፣ ከሲሊንደሩ የወጡ ሶስት ፒስተኖች ዙሪያውን ወድቀው ይታያል:: መሄጃ ሰንሰለቱ ሳይቀር ባንድ በኩል ተሰብሮ ተለያይቷል:: ሌላው ሳይቀር የአንድ ሴንትሜትር ውፍረት ያለው መከላከያ ብረት እንኳን የነዚህን ወታደሮችን ንዴት መቋቋም አልቻለም:: ምንም አይነት መፍቻ መሳሪያ እንዳልበራቸው አውቃለሁ:: ነገር ግን በላዩ ላይ ቁጥር 1935 የተቀረፀበት ታንክ ተበታትኖ ከምር ብቻ ሆኖ ቀርቷል::

እንዴት አድርገው እንደበተኑት እኔ ማስረዳት አልቻልኩም:: ሌላ የሚያውቅ ሰው ካለ ማስረዳት ይችላል:: ከዚህ በፊት ያገሬው ሰዎች ከባድ መሮዎች እስኪጣመሙ ድረስ ድንጋይ ሲሰብሩ አይቻለሁ::

በሚቀጥለው ቀን ካምፑ ውስጥ ጫጫታና ግርግር ነበር:: ሁሉም ሰው ሴቶችና አገልጋዮችን ጨምሮ ታንክ፣ አውቶሞቢልና የሞቱ ጣልያኖችን ምን እንደሚመስሉ ማየት ይፈልግ ነበር::

አውሮፕላኖች ተመላልሰው እየመጡ በምብ ያወርዱብን ነበር:: ነገር ግን ሁሉም ሰው በፍጥነት እንደ አይጥ በዛፍ ስር፣ ጫካ ውስጥ ወይም በድንጋዮች ጀርባ ስለሚደበቅ ያን ቀን ሰው ሳይጎዳ ዋለ:: በሌላ በኩል ግን ለግጦሽ ተሰቀው ስለነበረ በርከት ያለ ቁጥር ያላቸው እህዮች ተገደሉ:: በሬና ላሞች ከነበረው ቁጥራቸው ሰማንያ ስድስት አሥራ አራት ብቻ ቀሩ::

የንፁህ እንስሳት ግዙፍ ጭፍጨፋ ነበር::

የፊታውራሪ ሽፈራው ሰዎች ከእንዳባጉና አስራአምስት ኪሎ ሜትር ርቀት ከሚገኝ ጠላት ትቶት ከሄደው እንዳስላሴ ካምፕ አጠገብ ሰፍረዋል:: ያን ቀን ማታ ጀብዱ የሰሩ ሰዎች የማረኩትን እና እስረኞቻቸውን ይዘው ደጃች አያሌው ፊት እየቀረቡ ፎከሩ::

እዛገሮ በትልቅ ድንኳን መሀል ቦታ ወንበር ላይ ተቀመጡ:: እኛም አሽከሮቹን ጨምሮ ከኋላቸው ግማሽ ክብ ሠርተን ቆምን:: መጀመሪያ እንደአውሬ እርስ በርሳቸው በጩኸት የሚፎካከሩ ዘጠኝ ሰዎች መጡ:: ቀጥሎም እንዴት አድርገው የጣልያን ምርኮኞችን እንደያዙ በሥነስርአት ማሳየት ጀመሩ፤ አብረዋቸውም በፍርሃት የተዋጡ እራት ጣልያኖች ነበሩ:: ሁሰቱ ሰውነታቸው ላይ እራፊ ልብስ እንኳን አልነበራቸውም:: አንደኛው ራቁቱን ውስጥ ሱሪ ብቻ ነው ያደረገው:: አንደኛው ደግሞ ጫማ ካልሲ ኮት ወይም ኮፍያም አልነበረውም:: ጣልያኖቹ እዛው አመድ መስለው ቆመዋል



እነዚህ ያልሰለጡኑ ሰዎች ወይ ይሰልቡናል ወይ ከነህይወታችን ይበሉን ይሆን ብለው ማሰባቸው አልቀረም:: ነገር ግን እንደዛ ራቂታቸውን ቆመው ሲታዩ በዙሪያቸው በቆሙት በሙሉ የርህራሄ ስሜት ነበር የፈጠሩት::

ማራኪ ጀግኖቹ ድምፃቸው እስኪጎረንን ድረስ ጮኸው ሲያቆሙ ደጃዝማች ምርኮኞቹን ወደፊት አስጠሯቸው ምርኮኞቹ ደግሞ የፋሺስት ሰላምታ ሰጥተው ቆሙ::

ደጃች አያሌው ደግሞ "የለም" " አሁን ያላችሁት አቢሲኒያ ስለሆነ በኛ ደንብ ነው ሰላምታ መስጠት ያለባችሁ:: እንኳን ደህና መጣችሁ" አሉና ወደ መሬቱ ሲጠቁሙ ሰማስተርጎም ካለሁበት ብቅ አልኩ:: በፍርሃት ተውጠው ስለነበር እስካሁን ድረስ አላዩኝም ነበር:: ከዚያም ፊታቸው ፈካ ብሎ ወዲያውኑ ወደ መሬት ሰጥ ብለው እጅ ነሱ:: ቀና ሲሉ አይናቸው በደስታ እኔ ላይ ተተክሎ ሳያቸው እኔ ራሴ እንባዬ መጣ::

"ጣልያናዊ ነህ ወይ?" ሁሉም ባንድ ድምፅ

"አይደለሁም ግን ቋንቋችሁን እናገራለሁ"

"አሁን ሊገሉን ነው ወይ?"

"አትፍሩ ቃሌን እሰጣችሁዋለሁ በደንብ ነው የምትያዙት"

"ሀኪም ነህ ወይ?"

"አዎ"

"ግራዜ ሲኞር ዶክቶር" እናመሰግናለን ዶክተር ማለት ነው

ደጃዝማች ምርኮኞቹ ምግብ አግኝተው እንደሆን ጠየቁ:: የተቀቀለ የባቄላ እፍኝ ብቻ ነበር ለዛን ቀን የበሉት:: ልብስ እንዲመጣላቸው ትዕዛዝ ሰጡ:: እንዲቀመጡ ተፈቀደላቸውና ዳቦና የማር ብርዝ ቀረበላቸው:: ሰዎችን የማረኩት ሰዎች ምርኮኞቹን በሚያሳፍር ሁኔታ ስለበደሏቸው ተግሳፅ ተሠጣቸው፤ የወሰዱትን የሰዎችን ልብስና ጫማዎች በአስቸኳይ እንዲመልሱ ታዘዙ:: የወሰዱት ነገር ስነሱ የሚሆንም አልነበረም::

ከዚያ በኋላ ወታደሮች ጠላት ሰመግደላቸው መረጃ የሚሆን የራስ ቆብ፣ ሳንጃ፣ አውቶማቲክ መሳሪያ፣ ጥይት፣ መፅሀፎች፣ ሱሪዎች፣ ጫማዎች እና ሌላም ነገር ካለ ይዘው አቀረቡ::

ታንኩንና አውቶሞቢሎችን የሰበሩ ሰዎች ወደፊት እንዲቀርቡ ሲጠየቅ ከፍተኛ ጫጫታ ተፈጠረ:: እያንዳንዱ ሰው እነዚህን ጭራቆች ብቻውን

እንደማረከና እንደሰበረ የይገባኛል ክርክር ጀመሩ፡፡ ለዚህ ፋክክር መልስ ማግኘት አልተቻለም ያለው አማራጭ እነዚህን ጉረኞች ማስወጣት ነበር፡፡

ከመሀከላቸው ግን ከሰው ሁሉ በፊት ዘሎ የመጀመሪያው ታንክ ላይ ለመውጣቱ መረጃ ያለው ሰው ነበር፡፡ ያ ሰው ደግሞ ባላንባራስ ተሰማ* ነበር፡፡ ያ ሰው አገልጋዩን ቡና ያለ ጭስ አፍይ ብሎ ትእዛዝ በመስጠቱ እርባ ጅራፉን በኩራት ዋጥ አድርጎ የተቀበለው ነው፡፡

ደጃዝማች ምርኮኞቹን ጥያቄ መጠየቅ ስለፈለጉ ወደፊት እንዲቀርቡ ትዛዝ ሰጡ፡፡ ምርኮኞቹ አሁን ደፈር ያሉ እንዲያውም ደስተኞች ይመስሉ ነበር፡፡

ሥራቸው ምን ነበር? ከሶስት አንዱ መልከመልካም የአሥራ ዘጠኝ አመት ልጅ ያለበት መካኒኮች ነበሩ የቀረው ግን የጦር ሀኪም ነበረ፡፡ ሁሉም ማዕረጋቸው ማስተር ሰርጀንት ነበር፡፡

ጥያቄው እየተካሄደ እያለ ስድስት ሰዎች በማቋረጥ ከአንድ በኩል ሾል ያለ የበርሜል ቅርፅ ያለው ብረት ከደጃማች እግር ሰር በጥንቃቄ አስቀመጡ፡፡

"ጌቶች ይህንን ነገር አገኘነው የእሩብላ እንቁላል ይመስለናል ሰለዚህ ልናሳይዎ ብለን አመጣነው፡፡"

በቅፅበት እስከምችለው ድረስ ራቅ ብዬ ወደኋላ አፈገፍግኩ

እያሌው ቁጭ እንዳሉ በምቡን ለተወሰነ ጊዜ ካሰተዋሉ በኋላ ወደ አሥራ ዘጠኝ አመቱ ጣልያናዊ ዞር ብለው "አናንተ መካኒክ የሆናችሁት ይህንን ነገር ፍቱና ውስጡ ምን እንደሚመስል አሳዩኝ" አሉ

ወጣቱ ልጅ ደጃዝማቹን አየ፤ መልሶ በምቡን አየ፤ ቢጆሮው የሰማውን ነገር ያመነ አይመስልም፤ ከዚያም ወደኔ ዞር ብሎ "ዶክቶሬ እንዲያስተረጉሙ ላስቸግርዎት?" አለ

ቀጥሎ የሚናገረውን ነገር ከአይኑ መረዳት እችላለሁ

"ደስ ይለኛል፤ ግን ራሴን ከዚህ ቦታ ራቅ ማድረግ ብችል" አልኩኝ

ሳቅ በማለት "ኖን ሴ ፐሪኮሎ" አደጋ የለም አለ

---

**

*የባላምባራስ ተሰማ ታንክ መማረክ በሌላ ተጨማሪ መፅሐፍ ተዘግቧል። ባላምባራስ ተሰማ በአርበኝነት በአምባ ጊዮርጊስ አካባቢ በመንቀሳቀስ ጠላት ላይ ብዙ ጉዳት ያደረሰና ከዚያም የፈታውራሪ ማዕረግ እንደተሰጠው በዚህ መፅሐፍ በሰፊው ተፅፏል፡፡*

*Amedeo: A True story of love and War in Abyssinia; Sebastian O'Kelly*



ቀጥሎም "እኔ ለማለት የምፈልገው ይህን ብቻ ነው፡፡ እኛ ኢጣልያውያን ነን እርስዎ ደግሞ ጠላታችን ነዎት፡፡ በሀገራችን ለሀገር መሞት ክብር ነው፤ እኛም አስፈላጊ ከሆነ ለመሞት እዚህ ድረስ መተናል"

"አሁን ይህን በምብ ፍታ ብለው ትዕዛዝ ሲሰጡኝ ያለምንም ችግር በቀላሉ ላፈነዳው እችላለሁ፡፡ እራታችን እዚሁ አብረን እንፈነዳለን፤ ነገር ግን ኢጣልያ የጠላቶቿ ቁጥር ይቀነሳል በተለይ የእርስዎ አይነቱ"

"እንገደላለን ብለን እርግጠኛ ነበርን፡፡ ነገር ግን እርስዎ ከምንጠብቀው በላይ ነው የተንከባከቡን፡፡ ላደረጉልን ነገር ምስጋና ለማቅረብ ሰል ትዕዛዝዎን አልቀበለም፡፡"

እኔም ቀጥታ ጣልያናዊው እንደተናገረው አድርጌ በትክክል አስተረጎምኩ፡፡ ደጃማቹ ላይ ጥልቅ ስሜት እንደፈጠረም ማየት እችላለሁ፡፡ ከመቀመጫቸው ተነስተው ወታደሮቹን አመሰገኑ "ይህ ጀግንነት ነው፡፡ ይህ አርበኝነት ነው፡፡ እንደዚህ ወጣት ያለ እንደ ሺ ሰው ቢኖረኝ ማን ይቋቋመኝ ነበር?"

ወደፊት ተራመዱና የወጣቱን ጣልያናዊ እጅ ይዘው በሚያቃጭል ጣልያንኛ "ግራዚ" አሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ እያለን በምቡን ይዘው ለመጡ ለስድስቱ ሰዎች መልሰው እንዲወስዱትና መሬት ውስጥ እንዲቀብሩት ትዕዛዝ ተሠጠ፡፡

ጣልያኖቹም ወደ ዋሻ እንዲሄዱ ተደረገ፡፡ እኔም የሚያስፈልገውን ነገር ለማመቻቸት ሰል ተከትልኳቸው፡፡ አዲስ የታጨደ ሳር ወለሉ ላይ ተበትኗል፡፡ ሁለት መኝታ ከብርድልብስና አንሶላ ጋር ተዘጋጅቷል፡፡ የበራ ኩራዝ በአለቶች መሃከል ባለ ቦታ ተቀምጧል፡፡ ተጨማሪ ምግብና መጠጥ መጣላቸው፡፡ እስረኞችም ምግባቸውን እየበሉ ያጋጠማቸውን አጫወቱኝ፡፡

"**ቡም** !" ምንድነው? መድፍ ነው? ረጭ ሰላለ አዳመጥን ለአፍታ ያህል ነበር፤ ወዲያው ከውጭ በኩል ግርግርና ድምፅ ይሰማ ጀመር፤ እኔም በጨለማው ወደ ደጃዝማች እየሮጥኩ ሄድኩ " ምንድነው ነገሩ?"

"እንደሰማሽው መድፍ ነው፡፡ ጣልያኖች የኛን መስመር እያጠቁ ነው፡፡" አሉ ጫማቸውን አጠለቁና ጎራዴና ሽጉጣቸውን እየታጠቁ፡፡ ሰዎች ከደጃማች ትዕዛዝ ለመቀበል ወደ ውስጥና ውጭ ይመላለሱ ነበር፡፡ ከውጭ ትልቅ ጭንቀት ተፈጥሯል፡፡ ሰዎች ወዲያና ወዲህ ይሮጣሉ ይጣሩና ይጮሁም ነበር፡፡

"መጀመሪያ የሆነውን ነገር ብናጣራ አይሻልም" ወይ ብዬ ሀሳብ ሰነዘርኩ

"አዎ እሱ ጥሩ ሀሳብ መሰለኝ" አሉና አያሌው አምስት ወታደሮች ይዤ ወደ ጣልያናዊያን እስረኞች እንድወስድና በዚህ ግርግር ጥበቃ እንዲደረግላቸው እንዳደርግ ጠየቁኝ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ደጃዝማቹ ራሳቸው ወደአለንበት መጡና አየሳቁ ያ መከረኛ በምብ ነው ግርግሩን የፈጠረው እንጂ ሌላ ነገር አልነበረም ብለው ነገሩን፡፡

ወደኋላ ሙሉ ታሪኩን ሰማን፡፡ እነዚያ ስድስት ሰነፍ ሰዎች ጉድጓድ መቆፈሩን አልፈለጉም፡፡ ስለዚህ ሁሉም ተስማምተው በምቡን በእሳት ሰማቃጠል ወሰኑ፡፡ ወደ ማደሪያቸው በታም ሄዱና እሳት አንድደው ጓደኞቻቸው ቢያስጠነቅቋቸውም ችላ ብለው በምቡን እሳቱ ላይ አስቀመጡት፡፡ "የታባቱና!" የሚሆነውን ለማየት በአሳቱ ዙርያ ቁጭ አሉ፡፡

ቢያዩ ምንም ነገር አልሆነም፡፡ አንደኛው ተነስቶ እሳቱን ሲቆሰቁስ ቦምቡ ፈነዳ፡፡ በሚቀጥለው ቀን ሲታይ ብጫቂ ልብስና የተበጣጠሰ አካላቸው በየቦታው ዛፍና ቁጥቋጦ ላይ ተበትኖ ተገኘ፡፡ በሃምሳ ሜትር እቅራቢያ የነበሩ ስምንት ሰዎች ተጎድተዋል፡፡



# ምዕራፍ አሥራ አንድ

## ድል በእንዳባጉና

ተከዜን ሳንሻገር ስለ እንዳባጉና ጦርነት ወሬ እንደሰማን ሁለት ድሬሰሮችን ከሚያስፈልገው መሳሪያ ጋራ አስቀድሜ ልኬ ነበር፡፡ ደጃችዝማች የኔን መሄድ በጣም ይቃወሙ ነበር፡፡ በድል ስሜት ላይ ያሉ ወታደሮች እንደገና ደግሞ በጓደኞቻቸው ሞት በሀዘን ላይ ስለሆኑ ነጭ ሰው ካዩ ምንም ሳያወላውሉ ሊተኩሱበት ይችላሉ፡፡ ሁለት የኢጣልያ እስረኞች አንደኛው የቆሰለ ዶክተር በጦርነቱ ማግስት ጠዋት ጭንቅላታቸው ተቆርጦ ተገኝቷል፡፡ ባልተጠበቀ ሁኔታ አንዱ በማታ ሾልኮ ገብቶ የጓደኞቹን ሞት ተበቅሎባቸዋል፡፡

እንግዲህ ስንት የቆሰሉ ሰዎች መርዳት የምችልባቸው አራት ቀናት በከንቱ አለፉ፡፡ ምናልባትም ሕይወታቸውን ማትረፍ የምችልበት ሁኔታም ይኖር ነበር፡፡ ማምሻውኑ ከድሬሰሮቹ የመጣ መልከት ሥራውን ብቻቸውን ማከናውን ያልቻሉ መሆናቸውን ይገልፃል፡፡

በዚህ ምክንያት ነገሩ ተወሰነ፡፡ መሄድ አለብኝ

ደጃች አያሌው የመሄዴን ነገር ተጠራጥረዋል፡፡ ደግነቱ ከወዳጄ ከቀኛዝማች ንጋቱ ጥያቄ መጣ፤ ቀኛዝማቹ እራሳቸው ለኔ ደኅንነት ሀላፊነት እንደሚወስዱ ገለፁ፡፡ ጦርነት ላይ ነበሩ፡፡ ከነበራቸው መቶ ሰዎች ሀያ ሁለቱ ሞተዋል ወይም ቆስለዋል ለዚህ ነው እርዳታ የጠየቁት፡፡

በነጋታው በጠዋት ለመሄድ ወሰነናል፡፡ በመጨረሻም የተጎዱ ወታደሮችን በተቻለኝ አቅም መርዳት የምችልበት ሥራዬን መጀመር እችላለሁ፡፡ እስካሁን ምንም ነገር ማድረግ አለመቻሌ የኔ ጥፋት አልነበረም፡፡ ምንም እንኳን ሊደርስብኝ የሚችለው አደጋ ቢገባኝም ምናልባት ሙሉ በሙሉ ባይሆንም የነበረኝ የሙያ ግዴታ መንፈሴ ራሴን ለማዳን ከነበረኝ ፍላጎት በላይ ነበር፡፡

ለማንኛውም አሁን ለመሥራት ነፃ ነኝ። የቆሰሉትን ሰዎች ለመርዳት ባለመቻሌ ከሚሰማኝ አሳዛኝ ስሜትም ነፃ አሆናለሁ።

አራት ከበላን በኋላ ደጃች አያሌው በጦርነቱ ድል ስላደረጉ የተላከላቸውን ቴሌግራም በሚመለከት ወሬ አካፈሉኝ። በቴሌግራሙ ንጉሠ ነገሥቱ የምሥራች መልከት ልከዋል። ነገር ግን በሌላ በተከታይ ቴሌግራም ደግሞ ሌላ አዲስ ጥቃት እንዳይሰነዘር የሚል ትዕዛዝ አሰበት። አያሌው በመከላከል ብቻ እንዲቆዩ እና በጥንቃቄ የሚሆነውን ነገር እንዲከታተሉ። አያሌው የሰው ህይወት ያለአግባብ እንዲጠፋ እንዳያደርጉ። የተያዙት የኢጣልያ እስረኞች ባስቸኳይ ወደ ዳባት እንዲላኩና ከዚያም በአውሮፕላን አዲስ አበባ እንዲወሰዱ የሚል ነው።

"በግልፅ እንደሚታየው እኔው ራሴ ሪፖርት ላደረግሁት ድል መረጃ ይፈልጋሉ" በማለት አያሌው በሽርደዳ መልከ ተናገሩ።

ንጉሠ ነገሥቱ ጠቅላላው ምዕራብ ትግራይ በእንዳባጉና ጦርነት ምክንያት ነፃ እንደወጣ አስተማማኝ የሆነ መረጃ ደርሷቸዋል። ሁሉም የጠላት ምሽጎች ተወስደዋል፤ ጣልያኖችም ወደ አከሱም ሸሽተዋል። ያ ሁሉ ሆኖ ባለህበት ቆይ የሚል ትዕዛዝ ተላልፏል።

ደጃች አያሌው የተረበሹ ይመስላሉ። "የአዲስ አበባ ገዥዎች ምን ማለታቸው ነው?" ይህንን ትዕዛዝ ለወታደሮቼ ቢናገሩ አመፅ ይፈጠራል። ባገኙት ድል የተደሰቱት ወታደሮች ወደ አክሱምና አድዋ መገስገስ ነው የሚፈልጉት። በዚያን ጊዜ የኢጣልያ ቅኝ ግዛት ዋና ከተማ ወደ ነበረችው አስመራ ድረስ ካልሄዱ የሚያረካቸው ነገር አልነበረም። በዚህ አይነት መንገድ ነው የሚዋጉት እና አትቀጥሉ የሚባል ነገር ቢነገራቸው ወኔያቸውን እንደሚጎዳ ነው። ለምንስ አሁን ካውያው እንደጋለ በትኩሱ ጥቃቱ አይቀጥልም?

ምን ማለት አችላለሁ? በዚያን ጊዜ ደጃማቹ ትክክል እንደነበሩ አውቃለሁ ዛሬም ቢሆን ሰውየው ትክክል እንደነበሩ በተሻለ ሁኔታ አውቃለሁ። ነገር ግን የጦር አማካሪ የመሆን ሥልጣን አልነበረኝም። እነዚያ ሰዎች ከጦርነቱ ርቀው መናገሻ ከተማው ነው የተቀመጡት። በደንብ መረጃ እያላቸው ነገር ግን በጦር ግንባሩ ተሰልፈው የራሳቸውንም ሆነ የጠላትን አሰላለፍ በደንብ የሚያውቁ ሰዎችን አስተያየት ሳይቀበሉ ትዕዛዝ ማስተላለፍ እንችላለን ብለው ያስባሉ። የተመቻቸው እነዚህ ገዥዎች በነበራቸው የድንቁርና በራስ መተማመን ያለምንም ርህራሄ በአፍሪካ የመጨረሻዋን ነፃ ሀገር ዕጣ ፈንታ ወሰኑ።



ሌላው ዜና ደግሞ ምንም መልክት ሳይልኩ ራስ እምሩ በሌሊት በመኳዝ ከኛ ኪሎሜትሮች ራቅ ብለው ካምፕ አደረጉ። ጠዋት ፀሀይ ሳትወጣ እንዲገናኙ ጥያቄ ላኩ። አሁን ግን ራሳቸው አያሌው ዋሻ ድረስ ሊመጡ ነው። ለማሁ፤ ገረመኝም፤ ምንም አይነት እንኳን ደስ ያለህ ነገር የለም። ሰለ ድሉ እንኳን አንድ ቃል አልተናገሩም።

በነጋታው ጠዋት ከአሥራ ሁለት እጃቢዎች ጋራ ካምፑን ለቅቄ ሄድኩ። ቀኛዝማች ንጋቱ እንደተራ ሰው እያነከሱ በእግራቸው መጡ። እግራቸውን ሾህ ወግቷቸው ነበር። የነበሩበት በቅሎ ጦርነቱ ላይ ራሱን በጥይት ተመቶ ተገሎባቸዋል። የቆሰሉት ሰዎች ያሉበት ቦታ ለመድረስ በሙሉ ጦር ሜዳው መሀከል መሄድ ነበረብን። በቅርብ ጊዜ በሺ የሚቆጠሩ ሰዎች ለሞት ወይም ለድል በተዋጉበት መሬት ላይ መራመዴ እንግዳ ስሜት እንዲሰማኝ አደረገኝ።

ቀኛዝማች እየመሩን ሰለ ጦርነቱ ሰለተካሄደው ሁኔታ ከቀኛዝማቹ በሚደረግልኝ መግለጫ በቦታው የነበርኩ ያህል የመስማት እድል አጋጠመኝ።

ሰላዮቻችን እንደነገሩን ከሆነ በእንዳባጉና የነበረው ሜጀር ከጠቅላይ አዙ ምሽጉን ለቆ እንዲሄድ ትዕዛዝ ተሠጥቶት ነበር። የመጀመሪያው ቀን በሶስት ማለት ነው ሁሉም ካምፑን ጥለው ለመንቀሳቀስ ዝግጁ ነበሩ። ነገር ግን ሰላሳ ግመሎች ያሉበት ጓዝ ከአክሱም ሰሰተላከ ትዛዙ ተቀየረ፤ ሜጀሩም የሬዲዮ መገናኛዎችን እንደገና ሰቅሎ እስከ እሁድ ድረስ ለመቆየት ወሰነ።

*ያ ውሳኔ ግን መጥፊያው ሆነ*

ፊታውራሪ ሽፈራው ከደጃዝማች አያሌው ወደ ፊት እንዲሄዱ ትዛዝ በደረሳቸው ሰአት ከአክሱም ጓዝ መምጣቱንና ሜጀሩ እስከ እሁድ ድረስ ለመቆየት መወሰኑን ዜና አገኙ። በተጨማሪም ምሽጉ የሚጠበቀው በአንድ ሺ አምስት መቶ ከኤርትራ ከተመለመሉ ባንዳዎች ከመቶ ሃምሳ ነጮች ጋራና ሀያ አምስት መትረየሶች እያንዳንዳቸው ሁለት መትረየስ የተጠመደባቸው እስር ታንኮች መኖራቸውን መረጃ ይደርሳቸዋል። በተጨማሪ አራት የጭነት መኪኖች፣ አንድ አውቶሞቢል፣ መቶ የጭነት በቅሎዎችና ሰላሳዎቹ ግመሎች ነበሩ።

ወታደሮቹ ደግሞ የተናፈሰ የሰሙት ወሬ ነበር ይህም ከአከሱም የመጣው ጓዝ ማር ትሪዛ ጭኖ እንደመጣ ነው፡፡ በዚህ ዜና ምክንያት ወታደሮችን ይዞ መቆየት የማይቻልበት ሁኔታ ሲደርስ ምንም አልቀረውም፡፡ ፊታውራሪ ሽፈራው በሌሊት ተጉዘው የጠላትን መንገድ መዝጋት ምሽጉን ከቦ ከመቀመጥ የተሻለ ጠቀሜታ አለው ብለው አሰቡ፡፡

ፀሀይ ሳትወጣ በጠዋቱ ወታደሮቻቸውን በሀይዳ በኩል አድርገው በተከዜ ተንቀሳቀሱ፤ ሁሉም ሴቶችም አገልጋዮችም ጨምሮ ተከተሉ፡፡ እያንዳንዱ ሰው በሚቀጥለው ቀን ጦርነት እንደሚኖር አውቋል እና የቆሰለውን ለመርዳት የሞተውን ለመቅበር አብሮ መሄድ ፈልጓል፡፡

እነዚህ ሰዎች በተከዜ ወንዝና በገባሩ በማይቆላ በችግርና በመከራ ነው የተጓዙት፡፡ ባበዶ እግራቸው በጠጠሮች ላይ ጥቅጥቅ ባለ ጫካ ግማሹን ሌሊት ያለምንም የጨረቃ ብርሃን ነበር፡፡ የጠዋት ኮከብ ብቅ ሳትል ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ደረሱ፤ እሱም ከጣልያን ምሽግ አራት ኪሎሜትር ርቀት ነበር፡፡ ሀገሩን አቋርጠው ሲጓዙ ከጠዋቱ አሰራ አንድ ሰአት ላይ ቀጥታ ከጠላት ካምፕ በሰሜን አቅጣጫ በሚገኝ ከአንድ መጠነኛ ወራጅ ውሀ አጠገብ ለትንሽ ጊዜ አርፈዋል፡፡ በዚያ መንገድ ወደ ስልሳ ኪሎሜትር ርቀት የሚሆን ሲገሰግሱ አድረዋል ፡፡ ጓዝ የያዘው ክፍል ወደኋላ ቀርቷል፡፡

ጣልያኖች መኖራቸውን ካረጋገጡ በኋላ  መንገዱን በማቋረጥ ትንሽ ግንብ ቢጤ ሰሩና ጉድብ ቆፈሩ፤ አላማው ለጠመንጃ ተኳሾች መከለያ ሲሆን ጭነት መኪኖችና ታንኮችም እንዳይሸገሩ ለመከላከልም ነበር፡፡ ያሰቡት እንደዛ ነበር፡፡

ነገር ግን ግንቡም የግማሽ ሜትር ከፍታ ያለው የድንጋዮች ድርድር ጉድቡም ቢሆን ጥቅም አልነበረውም፡፡ ግማሽ ሜትር ስፋትና ግማሽ ሜትር ጥልቀት ነው የነበረው፡፡

ሁሉም ዝግጅት ካለቀ በኋላ  ሰዎች ቦታ ቦታቸውን ያዙና ፍፁም ፀጥታ እንዲኖር ታዘዘ፡፡ እንደሚባለው ከሆነ ግማሹ ጦር ወዲያውኑ እንቅልፍ ወስዶታል፡፡

ልክ ሁለት ሰአት ሲሆን የመጀመሪያው አላሽ ጦር የጫነ መኪና ከጣልያኖች ካምፕ አቅጣጫ መጣ፡፡ ትግስት ያጠራቸው የሽፈራው ወታደሮች በችኮላ ተኮሱ፡፡ ጠላት ጊዜ አግኝቶ ዞሮ መሸሽ ጀመረ፡፡ በዚህ ጊዜ ሁሉም የሽፈራው ጦር ቦታቸውን ለቀው ማጥቃት ጀመሩ፡፡ ፊታውራሪ ሽፈራው እራሳቸው ተነስተው በፈረሳቸው መንገዱን መዝጋት ነበረባቸው፤ አለዚያ



እነዚህ ስርአት የሌላቸው ወታደሮች እቅዳቸውን በሙሉ ሊያፈርሱባቸው ነው፡፡

ከምሽጉ የሚመጣውን ጥቃት ለመከላከል አንድ ሺ የሚሆኑ ወታደሮች ከካምፑ ግማሽ መንገድ የሚሆን ቦታ ጫካና ዛፎች ውስጥ ተደብቀዋል፡፡ ከምሽጉ አጠገብ ያለ ሜዳ ላይ አንድ አውሮፕላን አረፈ፡፡ አንድ ሰው ሲሮጥ ሄዶ ከፓይለቱ ጋር ለትንሽ ጊዜ ካወራ በኋላ  አውሮፕላኑ ተነስቶ ሄደ፡፡

በኋላ  እንደተረዳነው ቃኚው አወሮፕላን ከምሽጉ በተደረገለት ምልክት ነበር ያረፈው፡፡ ምክንያቱም ፓይለቱ የሚያስጠረጥር እንቅስቃሴ አይቶ እንደሆን ለመጠየቅ ነበረ፡፡ ፓይለቱ ግን ምንም አላየሁም ስላለ ሜጀሩም ትንሽ ቀማኛ ሽፍቶች ይሆናሉ ሰዎቹ ላይ የተኮሱት በማለት ተረጋጋ፡፡ ከዚያም ለቅኝት ታንክ ወጥቶ እንዲሄድ አዘዘ፡፡

ታንኩ በደረሰበት ጊዜ በመሪ ጦሩ አካባቢ እንቅስቃሴ ተጀመረ

"ተመልከት! ስትሄድ እንደ አሳማ ነው የምትወዛወዘው! ስማ እንደመቶበላ ደግሞ ትጮሃለች"

"ታንክ ነው?"

"እንዴታ!  ደደብ"

ከዛ ቀጥሎ ታንኩ እንዳይሰማቸው ማንሾካሾክ ጀመሩ፤ ምኑ ላይ ነው ጥሩ ቦታ ተኩሰን የምንገለው እያሉ ይወያዩ ነበር፡፡ ወዲያውኑ ከአዛዡ በተላለፈ ትዛዝ ታንኩ መስመራቸውን አልፎ እስኪሄድ ድረስ እንዳይተኩሱ ተነገራቸው፡፡

እንዲህ እንዳለ ታንኩ እየተወዛወዘ ጠጋ ማለት ቀጠለ፡፡ በመቶ ሜትሮች ርቀት የተሠጣቸውን ትዛዝ ጥሰው ትግስት ያጠራቸው ተዋጊዎች የተኩስ ውድድር ጀመሩ፡፡

ታንኩ ወዲያውኑ መልስ ተኩሰ በመስጠት በመንገዱ ዳርና ዳር ጉዳት አደረሰ፡፡ የፈሩና የደነገጡት ወታደሮች በየአቅጣጫው ሲበተኑ አንድ ሰው ብቻ ቀረ፡፡  ባላምባራስ ተሰማ ነበር፡፡ ከታንኩ በኋላ  ተስቦ ዘሎ አናቱ ላይ ወጣና ከዳኑን በሰደፍ እየደበደበ "ክፈት" እያለ ጮኸ፡፡

የታንኩ መሳሪያ ተኳሽ በድንጋጤ አደጋ መኖሩን ይርሳ አናውቅም ግን አውቶማቲክ መሳሪያውን መተኮሱን አቆመ፤ የታንኩ መግቢያም ተከፈተ፡፡ ወዲያውኑ ባላምባራስ በተከፈተው መግቢያ ተኮሰ፡፡

የታንኩ ሾፌር ቆመ፤ ወደኋላ ነድቶ ዞሮ መሄድም ሞከረ፤ ነገር ግን በሁለት ዛፎች መሀከል ተቀርቅሮ ቆመ፡፡  በዚህ ጊዜ ተሰማ የዚህን ጭራቅ

መግቢያ ቦታውን ስለተገነዘበ በሩን እንዴት እንደሚከፈትም አውቋል:: መግቢያውን ከፊት ያደርግና ጠመንጃውን ወደ ውስጥ አሾልኮ በፍጥነት ወደ ውስጥ ይተኩሳል::

ይህን ያዩ ሌሎች ወደ ታንኩ እየሮጡ መጡ፤ ሁሉም መተኮስ ይፈልጋል:: ሁሉም "አሳማው" ላይ ዘሎ መውጣት ይፈልጋል:: ታንኩ በድንገት መቃጠል ጀመረ:: የጋዝ መያዣው እሳት ተነሰቶበታል::

ከዚህ በኋላ ይህ ታንክ ያጋጠመው ዕጣ ለእንባቢ ግልፅ ነው::

በጣልያኖች ምሽግ ውስጥ ያሉ ሰዎች የሚሆነውን ሁሉ ቆመው ያያሉ፤ ማድረግ የሚችሉት ነገር አልነበረም:: ርቀቱ ለጠመንጃ የሚሆን አይደለም፤ መድፍ ደግሞ አልነበራቸውም:: ሁሉም ነገር በቅፅበት ስለሆነ ተጨማሪ ወታደር በጊዜው ከቦታው መድረስ አይችልም ነበር:: መንጋ ሰው ወደ ታንኩ ሲሮጥ ማየት ይችላሉ፤ ቁጥሩን ለመገመት ግን ዛፎችና ቁጥቋጦዎች ሙሉ እይታ ስለሚከለከሉ አስቸጋሪ ነበረ:: ማየት እስከቻሉበት ድረስ ግን የጥቁሮች ቁጥር የበላይነት ነበረው::

ሜጀሩ አጭር ውይይት ካደረገ በኋላ  ምሽጉን ከከበባ እየተከላከሉ መቆየት የማይታሰብ ሆነ:: ተጨማሪ ሀይል እስከሚመጣ ጊዜ ይወስዳል:: ያለው አማራጭ እየተዋጉ ጥሶ መሄድ ነው:: "የጠላት ቁጥር ከኛ በላይ ነው ነገር ግን ምን ፋይዳ አለው? ከታንክ ከአውቶማቲክ መሳሪያና በደንብ ከሰለጠነ ወታደር ጋር ሲወዳደር። ዛሬ እነዚህ አውሬ ሰዎች የኢጣልያ ወታደር ምን ማድረግ እንደሚችል ትምህርት ያገኛሉ:: ቪቫ ለ ዱቼ! ቪቫ ላ ኢጣልያ!"

አሁን ደግሞ አቢሲኒያኖች ከምሽጉ ወጥቶ ቁልቁለቱን እየተጠማዘዘ የሚወርድ የጠላት ሰልፍ ማየት ጀመሩ:: በአንድ ጊዜ ዘጠኝ ታንኮች በሰልፍ ወጡ፤ እነሱን ተከትሎ አራት ኮምፓኒ ወታደር ይወርዳል:: ከትንሽ ከፍተት በኋላ  ሜጀሩ ፈረስ እየጋለበ ወጣ፤ እሱን የተከተለው ደግሞ ጠቅላላው ስንቅና ትጥቅ ከተጨማሪ ሁለት ኮምፓኒዎች መሀከል ነበር:: ለፊታውራሪ ሽፈራው ወታደሮች ይህ በስነስርአት በሰልፍ የሚጓዝ ረጅም መስመር የሚያስደንቅ ዕይታ ነበር:: ስንቅና ትጥቅ ከፍሉ አራት የጭነት መኪናዎች፣ መቶ የጭነት ከብቶችና ሰላሳ ግመሎች አሉበት::

ስጊዜው ፊታውራሪ መላውን ጦራቸውን ወደኋላ ወራጅ ውሀ ወዳለበት ቦታ እንዲመለስ አደረጉ:: መሬቱ ዳጋታማና በቁጥቋጦ የተሞላ ነው:: በመንገዱ ቀኝ በኩል የዘንባባ ዛፍ ጥቅጥቅ ብሎ ያደገበት ሰፊ ጫካ ጥሩ



መጠለያ ሆነ ተገኘ:: እዚህ ሆነው ጠላትን ይጠባበቁ ጀመር፤ ሳይዘገይ ጠላት መድረስ ጀመረ:: ሁሉም ዘጠኝ ታንኮች ሜዳው ላይ በመስመር ተሰለፉና ወደ ዘንባባ ዛፍ ወዳለበት ጫካ ተኩስ ጀመሩ:: እግረኛው ደግሞ ወደ ቁጥቋጦዎች አቅጣጫ ማጥቃት ጀመረ::

መትረየስና ቀላል አውቶማቲክ መሳሪያዎች ተኩሱን ሲያቀልጡት ሁለት ቀላል አውቶማቲክ መሳሪያ ብቻ ለያዙት አቢሲኒያውያን ከአቅም በላይ ነበር:: በጫካ ውስጥ ተደብቀው የነበሩ ሁለት ሺ ሰዎች በድንጋጤ ወደ ራሳቸው ስንቅና ትጥቅ ጓዝ ወዳለበት መሮጥ ጀመሩ:: ሌሎች ደግሞ በየአቅጣጫው ይበተኑ ጀመር::

ሽፈራው ግን የሚሸሹ አይደሉም:: ያ ሁሉ ጥይት እየተተኮሰባቸው ፊትና ኋላ እየተመላለሱ ጥሩምባ እየነፉ ይጮሁ ጀመር "እናንተ ሴቶች ናችሁ? እኔ ራሴ እዚህ እንዳለሁ አታዩም? ወዴት ለመሄድ ነው የምታስቡት?"

በዚህ ሁኔታ አምስት መቶ የሚሆኑ ወታደሮች ማሰባሰብ ቻሉ:: ከነሱ ጋራ በመሆን ወደኋላ ተመልሰው በመንገዱ ቀኝ በኩል በአራት ጎጆዎች ተጠለሉ::

በዚህ ጊዜ ደግሞ ፊታውራሪ በላይ የተባሉ ሰው ከአሥራ ስምንት አመት ልጃቸው ጋራ በመሆን ሌላ ጦር አሰባስበው በጋራው ዙርያ በመሄድ ከጠላት ጀርባ ጥቃት ጀመሩ ጣልያኖችም በሁለት እጥፍ ተኩስ መሀከል ሆኑ::

እልከ አስጨራሽ ውጊያ ተካሄደ:: ሜጀሩ ቆስሎ በቃሬዛ ተጭኗል:: በጣልያኖች በኩል አንድ *ሻምበል፣ መቶ አለቃ፣ ሶስት የበታች መኮንኖችና ሁለት ሾፌሮች ሞቱ::

ጣልያኖቹ  እነሱ ላይ የተነጣጠረውን ትኩረት ለማስቀየር ብለው የጭነት ከብቶችን በየአቅጣጫው ለቀቋቸው:: ይህ ተንኮልም ሥራውን ሠራ:: አቢሲኒያኖቹ ከብቶችን በጥይት ተኩሰው ከጣሉ በኋላ  ሁሉንም ነገር ረስተው የተጫነውን ንብረት ለመውሰድ ጎራዴያቸውን እየመዘዙ ወደ ወደቁት ከብቶች መሄድ ጀመሩ:: በዚህ ጊዜ ጣልያኖች በብዙ ግፊት መንገዳቸውን እስከፍተው ወደ ፊት ጉዞ መቀጠል ጀመሩ:: ያም ሆኖ ከአደጋ ማምለጥ አልቻሉም::

---

***** *የሞተው ሻምበል ስም ኤቶሬ ክሪፓ ይባላል (Ettore Crippa) ሁለት ሰው ብቻ የሚይዙት የአስሩ ፊያት አንሳልዶ የሚባሉ ታንኮች አዛዥ ነበረ:: አሰከሬኑን ያገኘው አሜዲዮ የሚባለው የሊቢያ ፈረሰኞች አዛዥ ነው::*

*Amedeo: A True Story of Love and War in Abyssinia. Sebastian O'Kelly*

ፈርጥጠው የሄዱት ወደ ሁለት ሺ የሚሆኑት አቢሲኒያውያን ማስተዋል ጀመሩና እንዲያውም ጦርነቱ ላይ ያሉትን ጓዶቻቸውን ለመርዳት ወሰኑ:: አንድ ወገን በጋራው ዙሪያ በመሄድ ከጣልያኖቹ ጋር ሲፋጠጥ ጣልያኖቹን የግድ ወደኋላ ከመንገዱ ወደ ምእራብ አቅጣጫ ወደ ሚገኝ ከፍታ እንዲሸሹ አደረጋቸው::



ሜጀር ክሪኒቲ ቆስሎ በቃሬዛ ሲሄድ ከኢታልያኖች በኩል የተነሳ ፎቶግራፍ

ሌላው ወገን ደግሞ የጣልያኖችን ስንቅና ትጥቅ የሚያጓጉዘውን ክፍል ወረረው:: በጣም አለቃቂ ግን አጭር ጦርነት በኋላ ጣልያኖቹ እጃቸውን መስጠት ጀመሩ:: የቆሰለ ሰው ያያከመ የነበረው የኢጣልያ ዶክተር ከትከሻው ላይ በተሰነዘረበት ጎራዴ ምክንያት ወድቆ ህሊናውን ሳተ:: በኋላ እንደሰማነው ታስሮ እያለ ማታውኑ ተገደለ::

ሌላው የጦሩ ህክምና ባለሙያ የሆነውን ስላየ ጉድጓድ ውስጥ ተደበቀ በኋላም ተገኝቶ እስረኛ ሆኖ ተወሰደ::

ሌላው ጣልያናዊ በዱላ ጭንቅላቱ ላይ ተመቶ ህሊናውን ስቶ በሚቀጥለው ቀን ነው የነቃው:: የሱን ዕጣ ወደፊት እንነጋገርበታለን::

ሴቶችና ልጆች ስንቁንና ትጥቁን ሲረባረቡበት ወታደሮቹ ጠላትን ከጀርባ ለማጥቃት ገሰገሱ:: ሾፌሮቻቸው የተገደሉባቸው ሁለት የጭነት መኪኖች



በእሳት ጋዩ:: የቆሰሉ ጣልያኖችና ሌሎች መንገዱ ላይ የነበሩ በሙሉ ያለምንም ምርጫ ተገደሉ::

ጣልያኖች እንደገና በሁለት ተኩስ መሀል ተከበቡ:: አቢሲኒያኖቹ ከፍታውን ጥሰው ገብተው የተደበቁ ጣልያኖችን በሙሉ ገደሉ:: ብዙ መኮንኖች አብረው ተገደሉ:: የውሃ ጥሙ አስቸጋሪ ሆነባቸው ወኔያቸው ወደቀ:: ሁሉም ጦር ጋራው ላይ ተሰበሰበ መሳሪያቸውን ጥለው እጃቸውን ወደላይ አነሱ::

ይህንን ማድረግ አልነበረባቸውም::

ያልሠለጠኑት የኛ ጀግኖች የእጅ ወደላይ ማንሳቱ ምልክት አልገባቸውም:: እንዲያውም ጠላትን ለመምታት አጋጣሚ ፈጠረላቸው::

የጠፋው ህይወት ትልቅ ነው በተለይም ፊታውራሪ ሽፈራው ሶስት መቶ ሜትር ርቀት በሚገኝ ከፍታ ላይ ከወጡ በኋላ ተኩሱን ያቀልጡት ጀመር:: የያዙትን ቀላል አውቶማቲክ መሳሪያ ሲተኩሱ ጥይቱ በተንጣጣ ቁጥር ጎፈሬያቸው ይወዛወዝ ነበር::

ጣልያኖቹ የፈፀሙት ስህተት ወዲያው ገባቸው:: ወድያውኑ ሰንደቅ አላማቸውን አንስተው ከመኮንኖቻቸው ጋራ በመሆን መጮህ ጀመሩ:: "ቪቫ ላ ኢጣልያ" የመጀመሪያ ዙር ከተኮሱ በኋላ ሁሉም ወታደሮች ከጋራው ቁልቁል ወደ ሜዳው መሮጥ ጀመሩ:: ሜዳው ላይ የነበሩ ታንኮችና መኪኖችም መንቀሳቀስ ጀመሩ::

አቢሲኒያኖች ባሉበት ጋራ ላይ ግን አንድ ትንሽ ጥይት አንበሳውን ከነሸበቶ ጋማው መታቸው:: *ሽፈራው ወደቁ:: አማችየው የሚሉታቸው አባት አጠገባቸው ነበሩ ወደ መሬት አጎንብሰው "ልጄን!" አሉ ግን ወዲያውኑ ሁሉም ነገር እንዳቆመ ተገነዘቡ:: ፈጣን ሞት ነበር::

ይህ ሁሉ ሲሆን አብረው የነበሩት የንስሃ አባት መጡና "እኔ እሸከፈዋለሁ:: ሥራዬ ነው:: ግን የሱን ሞት ብድር የማይመልስ ሰው የተረገመ ይሁን" አሉ::

የስማንያ አመቱ የሽፈራው አማች ይህን አይነት ንግግር መስማትም አላስፈለጋቸውም:: በፍጥነት እንባቸውን ጠረጉ ሰውነታቸው ተንቀጠቀጠ አይናቸው ግን እንደ እሳት ይፋጃል:: ጉራዴያቸውን በቅፅበት መዘዙ::

---

*የፊታውራሪ ሽፈራውንና የባላምባራስ ተሰማን ገድል በሌላ መፅሀፍ በተመሳሳይ ሁኔታ ተፅፎ አግኝተናል (Haileselassie's War, Anthony Mockler)*

**ፊታውራሪ ሽፈራው አባከንትር ሽፈ ተብለው ይጠሩ ነበር*

የመሪው መሞት ወሬው ወድያው ተዛመተ። ዜናው በየመስመሩ ሲሰራጭ ተኩሱ ቆመ። ሁሉም ሰው ምንድን ነው የምናደርገው ብሎ የሚያስብ ይመስላል። በጣም አሰፈላጊ ደቂቃዎች በከንቱ አለፉ። ጣልያኖቹ አንድ ላይ ሆነው እያመለጡ ናቸው።

በዚህ ጊዜ ፊታውራሪ ነጋሽ እየሮጡ ወረዱ። ከአድሜያቸው ጋራና በንዴት የሚንቀጠቀጠው ጎራዴ የያዘውን እጃቸውን ከፍ አድርገው ወደ ላይ አነሱ።

"ልጆች!" አሉ በሚንቀጠቀጥ ድምፅ" ሽፈራው አልሞተም! ጠላት እንዳያመልጥ አዟችኋል። ተከተሉኝ!" ሰዎች መሰብሰብ ሲጀምሩ አይኑን ጨፍኖ እንደሚሄድ ሰው ወደ ፊት ገሰገሱ።

አምልጠናል ብለው ማሰብ የጀመሩት ጣልያኖች ከጀርባቸው የጭነት መኪናና ሁለት ታንኮች በያዘ በአግረኛ ኮምፓኒ የኋላ ጦር ሽፋን አግኝተዋል። ነገር ግን በንዴት እየከነፉ የመጡት አቢሲኒያውያን ደረሱባቸው። መኪናው ወዲያውኑ ተወረረ። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ከጥቅም ውጭ ሆነ። መኪናው ውስጥ የነበሩትን ሰዎች ለማዳን ተሰፋ በማድረግ ታንኩ ዞሮ መጣ። ወዲያውኑ ፊት ለፊት የነበሩ ሰዎች ታንኩ እናት ላይ ዘለው በመውጣት የታንኩን ሰዎችና ታንኩን ከጥቅም ውጭ አደረጓቸው። ሌላኛው ታንክ ራቅ ብሎ ሄዶ ወንዙን ለማቋረጥ በመሞከር ላይ እያለ መሻገሪያው ላይ ሲደርስ ተገለበጠ። ከታንኩ ስር እየተንፏቀቁ ከወጡ በኋላ ለመሸሽ የሞከሩት ሁለት ጣልያኖች በጥይት ወደቁ።

ኮምፓኒው ከወንዙ ማዶ ባለው ገደል ውስጥ አድፍጦ ተቀምጧል ነገር ግን ትንሽም ሳይቆይ መቋቋም አልቻለም። ይህንን የኢጣልያ የኋላ ጦር ለመርዳት ቆመው የነበሩ ሁለት ታንኮችም በአቢሲኒያኖቹ ከጥቅም ውጭ ሆኑ። ነጋሽ ጦሩን በጩኸት ያበረታታሉ "እነዚህ ውሾች እንዳያመልጧችሁ!" ለመበቀል ያላቸው ፍላጎት አልበረደም የድካም ስሜትም አልተሰማቸው። ጣልያኖቹ ራሳቸውን መከላከል እንዳለባቸው ተገንዘበዋል በፍጥነት በታንክ ጀርባ በድንጋዮችና በዛፎች ጀርባ መጠለል ጀመሩ።

እንደገና ከፍተኛ ውጊያ ተጀመረ። ሁለት ተጨማሪ ታንኮች ተደመሰሱ አንድ መኪና ከነሙሉ ጭነቱ በተዋጊዎች እጅ ወደቀ። ሌላ ታንክ በፍርሃት በፍጥነት ሲሸሽ የገደል ሥንጥቅ ውስጥ ተገለበጠ፤ መውጫያ ከዳኑም ሊከፈት አልቻለም። ከሁለት ቀን በኋላ ታንኩ ሲገኝ በውስጡ የነበሩ ሁለት



ጣልያኖች ጉድጓድ ተቆፍሮ ነው የወጡት። በነበራቸው አስከፊ ሁኔታ ኢትዮጵያኖቹ አዘኑላቸው በዚህ ምክንያት ህይወታቸው ተረፈ።

ጊዜው አሁን ከቀኑ አስር ሰአት ሆኗል። ሰሰው ልጅ ጥንካሬ ገደብ አለው ለአቢሲኒያኖችም ቢሆን። ሰሀያ አራት ሰአታት ምግብ የሚባል ነገር አልቀመሱም ከዚህ በኋላ ምንም ማድረግ የማይችሉበት ደረጃ ደርሰዋል።

ስለዚህ ስተወሰነ ጊዜ ቆም አሉ ጠላት በመስመር ከሁለት ታንከና ከአንድ መኪና ጋራ ሲሸሽ ተመለከቱ። ጠቅላላ አትኩሮታቸውን ወደ ራሳቸው አድርገው የቆሰለውን መርዳት ፀሀይ ሳትገባና ጅቦች ሳይመጡ የሞቱትን መቅበር ጀመሩ።

"ስማ! ምንድነው?"

ከደቡብ አቅጣጫ አቧራው እንደደመና ትጉልል ብሎ ይታያል። ቀጥሎም በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ሲጨፍሩ ይሰማል።

አንበላው! እንበለው ደም!
አሃ!
አንበለው!
አሃ!
አንበለው ደም!

በመጨረሻም ደረሱ። የፊታውራሪ ተሻገር ሰዎች ነበሩ፤ ከምዕራብ በኩል ነው የመጡት። የጦርነት ድምፅ ሰምተዋል። ጠላት የት እንዳለ ማወቅ ይፈልጋሉ።

ጣልያኖቹ እየሸሹ እንደሆነ ተነገራቸው።

አንዳንድ የሽፈራው ሰዎችም ወኔያቸው እንደገና ተነስቶ እነዚህን አዲስ የመጡትን ተከተሉ

ጭፈራው ቆመ። አሁን በሙሉ ጉልበታቸው ከጠላት ኋላ መሮጥ አለባቸው፤ እያንዳንዷ ደቂቃ ወሳኝ ነበረች። ጠላት ላይ መድረስ ነበረባቸው፤ እንዳሰቡትም ተሳካላቸው።

በተራራው ዙሪያ ሮጠው ቀስ እያለ ከሚጓዘው የጣልያን ጦር ጋራ ተገናኙ። ጣልያኖቹ ደክመዋል፤ ከጠላት እጅ አምልጠናል ብለው አስበው ነበር። ጎራዴውን እያወዛወዘ በጩኸት የሚመጣውን አዲስ የጠላት ሀይል ሲያዩ ወኔያቸው ቢሰበር ሰው ሊረዳው የሚችለው ነገር ነው።

ይህ ቀን ማቆሚያ የለውም?

ነገር ግን ጀግኖቹ የሚያቆሙ አይነት አልነበሩም:: መጠለያ የለም፤ መሬቱ ሜዳማ ነው ሳሩም በእሳት ተቃጥሏል:: አማራጭ ስላልነበር ጣልያኖቹ መሬት ላይ ተጋድመው መተኮስ ጀመሩ:: ወድያውኑ ደግሞ ዘለው ይነሱና የሚችሉትን ያህል ነብሳቸውን ለማዳን ይሮጣሉ:: እንደዚህ እያደረጉ እየደጋገሙ የሚችሉትን ያህል ራቁ::

አቢሲኒያኖች ደግሞ ቀደም ብሎ እንደሆነው ሁሉ ትኩረታቸውን መኪናው ላይና ታንኮቹ ላይ አደረጉ:: ብዙ ጊዜም ሳይወስድ ቁጥጥር ስር አደረጓቸው *ሁለት የኢጣልያ ታንከኞች ብቻ አመለጡ::

ማሳደዱም ቀጠለ በዚያው ልክ ደግሞ ከጣልያኖች ጋራ የተሰለፉት የኤርትራውያኑ ጉብዝና የተሞላበት መከላከል እስከ ማይ ሚኒ ወንዝ ድረስ ቀጠለ:: እዚያ ሲደርስ ቆመ:: ምክንያቱም ጨለማው እየመጣ ነበር:: አቢሲኒያኖች ደግሞ ከዚያ በላይ መግፋት አልቻሉም:: ምክንያቱም የአንዳ ሰላሴ የጠላት ካምፕ ማዶ እንዳለ ያውቁ ነበር::

ያን ቀን ከረፋዱ በኋላ  የጠላት በምብ ጣይ አውሮፕላን በጦር ሜዳው ላይ እያንዣበበ ትንንሽ በምቦች እየጣለ አውቶማቲክ መሳሪያም ይተኩስ ነበር:: አቢሲኒያኖች ደግሞ ከጠላት ጋራ ግብግብ ይዘው ጉዳይም አልሰጡትም ነበር:: ተቀላቅሎ ስለነበር ለበምብ ጣይ አውሮፕላኑ ጠላትና ወዳጅ መለየት ስላልቻለ ብዙ ጉዳት አላደረሰም:: በኋላ  ግን የአቢሲኒያኖች ስንቅና ትጥቅ ክፍሉን አግኝቶ ብዙ ጥይትና ሌላም ጓዝ በእሳት በምብና በሚነደው ሳር ምክንያት ከጥቅም ውጭ ሆነ::

---

** ያን ቀን ካመለጡ የኢጣልያ ወታደሮች አስራ አለቃ ብሩኖ የሚባል እንደነበረና ታንኮቹን የማይረቡ ናቸው ብሎ እንዳማረረ ተጠቅሷል:: አስር አለቃው በአካባቢው ከነበሩ የሊቢያ ስፓሂ ወታደሮች ጋር እንደተደባለቀ ተዘግቧል::*
*Amedeo: A True Story of Love and War in Abyssinia. Sebastian O'Kelly*

*ከዚህ ፅሁፍ ታሪክ በመነሳት ከጣልያኖች ጋራ የመጀመሪያውን ጦርነት ያካሄዱት የደጃዝማች አያሌው ተከታዮች ከሆኑ፤ በዚህ ጦርነትም ታንክ የተደመሰሰበት ከሆነ፤ የመጀመሪያውን ታንክ የማረከው የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ባላምባራስ ተሰማ መሆኑ ነው:: ይህንን ግን አንባብያንና የታሪክ ባለሙያተኞች በአዎንታ ሆነ በአሉታ እንዲነጋገሩበት እንጋብዛለን::*



# ምዕራፍ አሥራ ሁለት

## ቁስለኞችን ማከም

በታህሳስ ስድስት በእንዳባጉና የተደረገው ጦርነት ምዕራቡን የትግራይ ክፍል ከጣልያኖች ቅኝ ግዛት አስለቅቋል:: ገና በሰቲት አካባቢ ነው የተባለው ግን ድንገተኛና ሀይለኛ ጥቃት ያካሄደው የአቢሲኒያ ጦር ሌሎች በአዲያቦ፣ ሽሬ እና ዛና የሚገኙ ስድስት የጣልያን የጦር ካምፖችን አስጊ ሁኔታ ፈጥሮባቸዋል:: ስለዚህ ጣልያኖቹ በስባት ማታውኑ ጓዛቸውን ጠቅልለው በጥንቃቄ ወደ ዋናው ካምፕ አክሱም ገቡ::

በአቢሲኒያኖች በኩል የደረሰው ጉዳት ግን ከፍተኛ ነበር:: ሶስት መቶ ሰማንያ ሁለት ሰዎች ተወዳጁንና ጀግናውን ፊታውራሪ ሽፈራውን ጨምሮ ሞተዋል:: ሁለት መቶ ሃምሳ ስድስት ሰዎች ደግሞ ቆስለዋል::

አቢሲኒያኖቹ ለህይወት ስለማይሳሱ ከተገኘው ውጤት ጋራ ሲወዳደር ጉዳቱን የከፋ አላደረጉትም:: በችኮላና በድንቁርና ታንኮችን ባያጠቁ ኖሮ የደረሰው ጉዳት ከዚህ ያንስ ነበር :: ያም ሆኖ በዚህ ሁኔታ ትልቅ ድል ነው ያገኙት ለድፍረት የሚሆን የጦርነት ልምድም አገኙ:: እነዚህ ጭራቆች (ታንኮችን ማለት ነው) ሊደፈሩ የሚችሉ መሆናቸውን ተገነዘቡ::

በጣልያኖች በኩል ደግሞ ስባት መኮንኖች፣ ሃያ ሶስት ነጭ ወታደሮች፣ አርባ ስምንት የኤርትራ ተወላጆች መኮንኖችና መቶ ሃያ ስባት ባንዳ ወታደሮች ሞተውባቸዋል:: የቆሰሉት ቁጥር ሰላሳ ብቻ ነው ተብሎ የተዘገበው::

የዚህ የተሰጠው ቁጥር አጠራጣሪ ነበር ምክንያቱም ሃምሳ አንድ የነጭ ወታደሮች ሜዳው ላይ ሞተው ተገኝተዋል:: ስንቶቹ መኮንኖች እንደሆኑ ማወቅ አይቻልም ነበር:: ምክንያቱም ልብሳቸው ስለተውሰደ ራቁት ነበሩ:: ልብስ በጣም ተፈላጊ ነበር::

ሁሉም ሞተው የተገኙት አቢሲኒያውያን የጦርነቱ ለት ማምሻውን አጠገብ ባለ ቤተክርስቲያን በዘመድና ወዳጆቻቸው ተቀበሩ::